የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993
ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቁጽ 1 ቁጥር 12 ሰኔ 30/2015 ዓ.ም

ሙስና ህዝቡ ከልቡ ካልታገለ በስተቀር በቀላሉ የምንለቀቀው ጉዳይ አይደለም- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አህመድ

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 28ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሙስና ህዝቡ ከልቡ ካልታገለ በስተቀር በቀላሉ የምንላቀቀው ጉዳይ አይደለም ብለዋል።

ጠቅላይ ሚንስትሩ ቀጥለውም፤ እውነት ምክር ቤቱም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙስና እንዲጠፋ ይፈልጋሉ ወይ? ሲሉ ጠይቀዋል። ሙሰኛ ሲያዝ ለምን ተያዘ ተብሎ ተቃውሞ የሚሰማበት፤ ሙሰኛውም ሚዲያ እና ባለስልጣናት በገንዘብ ገዝቶ የሚንቀሳቀስ አደገኛ ሁኔታ መኖሩን አንስተዋል።

ሙስና ያለው ነዳጅ ውስጥ ነው፤ ሙስና ያለው መሬት ውስጥ ነው፤ ሙስና ያለው ግዥ ውስጥ ነው ተብሎ የተጀመረው ሙከራ በሙሉ ከፍተኛ ተቃውሞ ይነሳበታል ብለዋል።

ሙስናን ከልብ የምንጠየፍ ከሆነ መሬት ላይ፣ ግዥ ላይ እና የፀጥታ ተቋማት ላይ ጨክነን ካልወሰን በስተቀር አንፈታውም ሲሉ ተደምጠዋል።

ያም ቢሆን በርካታ ተጠሪጣሪ ተጠያቂ መሆኑን፤ ይህ ሂደት ወደፊትም እንደሚቀጥል ገልፀው፤ ሙስናን ህዝቡ ከልቡ ካልታገለ በስተቀር በቀላሉ የምንላቀቀው ጉዳይ እንዳልሆነ በአፅንኦት ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ከፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ለተነሳላቸው ጥያቄ ሲያብራሩ "ምክር ቤቱ እንዲረዳልኝ የምፈልገው ከህዝብ አንድ ብር አልሰርቅም"ሲሉ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም በሁሉም ከተሞች ህገወጥ ግንባታዎች ይፍረሱ የሚል ስምምነት አለ፤ የዋህ የሆኑ ዜጎች፣ አታላይ የሆኑ ደላሎች፣ ሙሰኛ የሆኑ የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ተጋግዘው እና ተደጋግፈው የህዝብና የመንግስትን መሬት እየዘረፉ ስለሆነ!" በጋራ መታገል አለብን ብለዋል።

ብዙ ሌባ በውስጣችን አለ፤ ብዙ አጭበርባሪ እና ብዙ ንፉግ በውስጣችን አለ፤ ገና ብዙ ጥረት ይጠበቅብናል ሲሉ ተደምጠዋል።

ኮሚሽኑ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሥነምግባር ክትትል እና የጥቅም ግጭት መከላከል ረቂቅ ደንብ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ አካሄደ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሥነምግባር ክትትልና የጥቅም ግጭት መከላከል ረቂቅ ደንብ ያዘጋጀ ሲሆን፤ በረቂቅ ደምቡ ላይ ሚንስትሮች፣ የሚዲያ ኃላፊዎች፣ የፌደራል ተቋማት ኃላፊዎች እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ተወካዮች በተገኙበት በአዲስ አበባ ኃይሌ ግራንድ ሆቴል ውይይት አካሂዷል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) በመድረኩ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ሙስና እንደ ሀገር ትልቅ አደጋ ደቅኖ ያለ የሰላምና የልማት እንቅፋት መሆኑን ገልፀው፤ ችግሩን ለመከላከልም መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን አረጋግጠዋል።

በዋነኛነት የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ሙስናን እንዲዋጉ ታስቦ ረቂቅ ደንቡ መዘጋጀቱንም ነው ያስገነዘቡት።

በጠቅላይ ሚንስትር ፅ/ቤት የካቤኔ ጉዳዮች ሚንስትር ዲኤታ ክቡር ተስፋዬ ዳባ በበኩላቸው የመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች የመወሰን ስልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ፤ ይህን ኃላፊነት ስነምግባራዊ አመራር ተላብሰው እንዲወጡ ስለሚጠበቅባቸው የጥቅም ግጭት መከላከል ደንቡ መዘጋጀቱን ገልፀዋል።

አስተያየት ሰጪዎች በበኩላቸው የተወሰኑ ማሻሻያዎችን በማከል በፍጥነት ወደ ተግባራ መገባት እንዳለበት አንስተዋል። ትልቁ ተግዳሮት አተገባበር ላይ በመሆኑ ኮሚሽኑ ለትግበራው አበክሮ መስራት እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል።

የወረዳ ዋና ስራ አስፈጻሚና ምክትላቸው ሙስና ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ ተያዙ

ገጽ 3

«በአደኩበት አካባቢ፣ ከዚያ ሰው ፈቃድ ውጪ የሰውን ገንዘብ መውሰድ ትልቅ ሀጥያት ነው» - አቶ አማረ ታደሰ

ገጽ 14

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ የትብብር ስምምነት ተፈራረሙ

የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ላይ የትብብር ስምምነት ተፈራረሙ።

በጋራ ከሚሰሩባቸው ጉዳዮች መካከል በመንግስት ተቋማት ውስጥ የተጠያቂነት፣ የመልካም አስተዳደር እና የግልፀኝነት ስርዓት ማስፈን እንዲቻል የሙስና እና ብልሹ አሠራሮች ሊከሰቱባቸው በሚችሉ ተቋማትና የስራ ዘርፎች ላይ ተከታታይ የሆኑ ጥናቶችን በጋራ ማከናወን፣ ከሌሎች አጋርና ደጋፊ አካላት ጋር በመቀናጀት የስምምነቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን ለመንግስት ተቋማት በትብብር መስጠት እና በወንጀል ተግባራት ላይ ጥቆማዎችን ማድረግን ጨምሮ አስፈላጊ በሆኑና በጋራ ሊያሰሩ በሚችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ጠንካራና ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋት እንዲሁም የመልካም አስተዳደር፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት እውቅና የሚያገኙበትን መንገድ በጋራ ማመቻቸት ይገኝበታል።

ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) በስምምነቱ ወቅት እንዳሉት ተቋሙ ንፁህ የሆነ ሥራ መሥራት እንዳለበት አስረድተው፣ በተገኙ የኦዲት ግኝቶች ላይ በቀጣይ ሩብ ዓመት ዕርምጃ በመውሰድ ለሌሎች ተቋማት ምሳሌ ለመሆን እንደሚሠሩና በዚህ የማጣራት ሒደት የሙስና ድርጊት ከተገኘ ዕርምጃ እንደሚወስድ አስታውቀዋል።

ኮሚሽነሩ አክለውም የኮሚሽኑ ሥራ መረጃና ዕውቀት መር በመሆኑ ተቋማት ሰፋ ያሉ የሙስና ሥጋት ጉዳዮችን ቀድሞ በመለየት የመከላከል ሥራ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፣ በቀጣይ የአገር ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የቅድመ መከላከል ሥራ እንደሚከናወን አስረድተዋል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወ/ሮ መሠረት ዳምጤ በበኩላቸው ሁለቱ ተቋማት በጋራ የሚሰሩባቸው ጉዳዮች መኖራቸውን ጠቅሰው፣ ብልሹ አሰራርን በመከላከል እና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ የጋራ ስምምነቱ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አመላክተዋል።

በጋራ ትብብር የሚከናወኑ ተግባራት አፈጻጸሞችን በሁለት ወር አንድ ጊዜ በጋራ እንደሚገመግሙ የተገለፀ ሲሆን፣ አስፈላጊ ከሆነም መግለጫዎችን እና ሌሎች ተግባራን በየጊዜው እየተገኙ እንደሚያከናውኑ ተብራርቷል።

የመንግስት እና የሕዝብ ኃብት ለታለመለት ዓለማ ባለመዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራር የብሔራዊ ስጋት እየሆነ የመጣ በመሆኑ የፍትህ ተቋማት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት አለባቸው - የተከበሩ አቶ ክርስቲያን ታደለ

የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ26ኛ መደበኛ ስብሰባው፤ የኡዲት ግኝቶች በሚታይባቸው ተቋማት ላይ ማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባ አሳስቧል። ምክር ቤቱ በውሎው የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የ2014 የፌደራል መስሪያ ቤቶች የፋይናንስ ሕጋዊነትን የከዋኔ ኦዲት አፈፃፀም ሪፖርትን አድምጧል።

የምክር ቤቱ አባላትም የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ባመላከታቸው የገንዘብ ግኝቶች የሚመለከታቸው የፍትህ ተቋማት የእርምት እርምጃ መወሰድ እደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል።

እንደሀገር ከፍተኛ የሆነ የበጀት ዕጥረት እያጋጠመ በመሆኑ የሒሳብ አያያዝን መመሪያ እና ደንብን ተከትለው ተቋማት እንዲሰሩ የምክር ቤቱ አባላት አሳስበዋል።

የመንግስት ወጪ፣ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ክርስትያን ታደለ የመንግስት እና የሕዝብ ኃብት ለታለመለት ዓለማ በትክክል እንዲውል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እያደረገ ያለውን ጥረት አበረታተዋል። የከዋኔ ኦዲት ስራዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ በማድረግ የሪፖርቱን ተአማኒነት እና ተቀባይነትን ማረጋገጥ እንደሚገባም ሰብሳቢው አመላክተዋል።

አስፈጻሚው አካል ለኦዲት ግኝቶች ትኩረት ባለመስጠት የገንዘብ የመመለስ ምጣኔው በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተቋማትን በመቆጣጠር እና ተጠያቂነትን ማስፈን እንደሚጠበቅበት የተከበሩ አቶ ክርስቲያን ጠይቀዋል። የመንግስት እና የሕዝብ ኃብት ለታለመለ ዓለማ እያዋለ ባለመሆኑ ሙስና እና ብልሹ አሰራር የብሔራዊ ስጋት እየሆነ የመጣ በመሆኑ የፍትህ ተቋማት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸው የተከበሩ አቶ ክርስቲያን ማሳሰባቸውን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በፌስቡክ ገፅ አጋርቷል።

የፌደራል የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ዋና ኦዲተር ክብርት ወ/ሮ መሰረት ዳምጤ በ86 የመንግስት መስሪያ ቤቶች 6 ቢሊዮን 838 ሚሊዮን 886 ብር ተመላሽ እንዲደረግ ሙያዊ አስተያየት ቢሰጥም፤ 0.65 በመቶው ብቻ ተመላሽ በመደረጉ የሚፈለገውን ለውጥ እያመጣ እንዳልሆነ በሪፖርቱ አመላክተዋል።

በተያያዘ መረጃ የፌደራል ዋና መስሪያ ቤት የ2014 በጀት ዓመት የጥሬ ገንዘብ ጉድለትን በሚመለከት ባደረገው ኦዲት በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ከ172 ሺህ ብር በላይ እና በሞያሌ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ በድምሩ ከ1 ሚሊዮን 3 መቶ ሺህ ብር በላይ ጉድለት መገኘቱ ተረጋግጧል ሲሉ ዋና ኦዲተሯ ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ አስታውቀዋል።

ጉድለቱ በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲደረግ፣ እንዲሁም የተሰጣቸውን ኃላፊነት ዘንግተው ገንዘቡን ባጎደሉ ሰራተኞች ላይ ተገቢው አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት መሰጠቱን ዋና ኦዲተሯ በሪፖርታቸው ገልጸዋል።

በተወሰኑ የመንግስት እና የሕዝብ ኃብትን ባባከኑ የሥራ ኃላፊዎች ላይ የገንዘብ ቅጣት እና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በገንዘብ ሚኒስቴር አማካኝነት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ዋና ኦዲተሯ ገልጸዋል።

የሙስናን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉም ዜጋ የፀረ-ሙስና ትግሉ አካል ሊሆን እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ሙስናን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁሉም ዜጋ የፀረ-ሙስና ትግሉ አካል ሊሆን እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጠይቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነምግባና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሴክተር፣ ከክፍለ ከተማ እና ከወረዳ ስነምግባር መኮንኖች ጋር በስነምግባር መከታተያ ክፍሎች አሰራርና አደረጃጀት ዶንብ እና የስነምግባር ግንባታ እና ሙስናን መከለከል ደንብ ላይ ዉይይት አካሄዷል።

ኮሚሽኑ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝም ገልጿል።

ማንኛውም ተገልጋይ አገልግሎት ፈልጎ በሚሄድበት ተቋም ላይ አገልግሎቱን በገንዘብ መግዛት እንደሌለበትና መብቱን ማስጠበቅ እንደሚገባ ኮሚሽኑ ማስታወቁን አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ ዘግቧል።

በሀገር ደረጃም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ የሙስና ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን የገለጸው ኮሚሽኑ፥ ይህን ችግር ለመወጣት ሁላችንም ሀላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል ብሏል።

በሀብትና ገቢ ምንጭ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዲሁም ጥቅም ግጭትን የመለየት ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ተካሄደ

በሀብትና ገቢ ምንጭ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዲሁም ጥቅም ግጭትን የመለየት ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ተካሄደ።

የፌደራል ሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለመረጃ ሰጪ ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት በሀብት ምዝገባ ስራ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አካሂዷል።

መድረኩም በኮሚሽኑ እና በመረጃ ሰጪ ተቋማት መካልከል ፈጣን ተአማኒነት ያለው እና ሚስጥራዊነት የተጠበቀ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር የሚያስችል ነበር ።

በመድረኩ እንደተገለፀው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሀብት ምዝገባ ተግባር የጀመረችው በ2002 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 668/2002 ሲሆን ኮሚሽኑ ተሻሻለው የማቋቋሚያ አዋጁ 1236/2013 እና በአዋጅ ቁጥር 668/2002 መሠረት የተሿሚዎች፣ የተመራጮችና ምዝገባው ሚመለከታቸውን የመንግሥት ተቋማት እና ህዝባዊ ድርጅቶች ሠራተኞችን ኮሚሽኑ ሀብት የመመዝገብ፣መረጃ ተደራሽ ማድረግ፤ የመረጃ ትክክለኛት የማረጋገጥ እና የጥቅም ግጭትን የመከላከል ሥልጣንና ኃላፊት የተሰጠው መሆኑ ተመልክቷል።

በዚሁ መሠረት ኮሚሽኑ በቀጣይ የጥቅም ግጭት የመከላከል ተግባራትን በሰፊው እንደሚያከናውን ተጠቅሷል።

የወረዳ ዋና ስራ አስፈጻሚና ምክትላቸው ሙስና ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ ተያዙ

በአዲስ አበባ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ዋና ስራ አስፈጻሚና ምክትላቸው በመስሪያ ቦታ አሰጣጥ ተደራድረው ሙስና ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ መያዙን ፖሊስ አስታወቀ።

የጉለሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አዛዥ ረ/ኮሚሽነር ፋሲካ ፈንታ እንደገለጹት፥ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 ከስራ ዕድል ፈጠራ ላይ ብሎክን መሰረት በማድረግ የተፈጠረ የስራ እድል ላይ ከተጠቃሚ ወላጅ ጋር በጎንዮሽ የተሻለ የመስሪያ ቦታ እናሰጣለን በማለት የተጠቃሚዋን ወላጅ አባት ብር ካልሰጠሽን ልጅህን ከስልጠና እናወጣታለን፥ የስራ እድልም አይፈጠርላትም በማለት ወላጅ አባቷን በማስፈራራት ልዩ ስሙ 6 ኪሎ አከባቢ ልዩ አዲስ ሆቴል 50,000 (ሀምሳ ሺህ ብር) ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ መያዙን ፋና ዘግቧል።

እጅ ከፍንጅ የተያዙት ግለሰቦች ነኛ የጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ዋና ስራ አስፈፃሚ አያናው አስራት እና 2ኛ የወረዳው ምክትል ስራ አስፈጻሚና የስራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ እዮብ አፈወርቅ 50,000 ብር በዛሬው ዕለት ከቀኑ 10:30 ሰዓት ሲቀበሉ ክትትል በማድረግ በጸጥታ ሃይሎች እጅ ከፍንጅ መያዛቸው ተገልጿል።

በዚህም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ገብተው ተጨማሪ ምርመራ እየተደረገባቸው እንደሚገኝ ተገልጿል።

የሶማሌ ክልል የመንግሥት ተሿሚዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ሰራተኞች የሀብት ምዝገባ እየተካሄ ነው

የሶማሌ ክልል የመንግሥት ተሿሚዎች፣ የምክር ቤት አባላትና የሰራተኞች የሀብት ምዝገባና ማሳወቂያ መርሃ-ግብር በጅግጅጋ ከተማ ተካሄደ።

በሀብት ምዝገባ መርሃ ግብሩ ላይ የክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ወይዘሮ አያን አብዲ፣ የክልሉ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አብዲ ወሊ፣ ተሿሚዎችና የምክር ቤት አባላት ሀብታቸውን አስመዝግበዋል።

በተጨማሪም የክልሉ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮችና ሰራተኞችም ሀብታቸውን እያስመዘገቡ መሆኑን ኢዜአ ዘግቧል።

የሀብት ምዝገባው እየተካሄደ ያለው ባለፈው ዓመት በክልሉ ምክር-ቤት የፀደቀውን አዋጅ ቁጥር 215/2014 ተፈፃሚ ለማድረግ መሆኑም ተመልክቷል።

በሀብት ምዝገባው ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረት፣ የግለሰቡና ቤተሰቦቹ የገቢ ምንጭ እንዲሁም በውርስ የተገኘ ቤትና ድርጅት መካተቱ ተገልጿል።

በፕሮጀክት ሥራ አመራር፣ አስተዳደርና የሙስና መከላከል የአቅም ግንባታ ስልጠናዊ ውይይት ተካሄደ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዳማ እና በሀዋሳ ከተሞች ለጤና፣ ለግብርና፣ ለፋይናንስ እና ለከተማና መሠረተ ልማት ዘርፎች ስር ለሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ለአራት ቀናት የቆዩ የፕሮጀክት ሥራ አመራር፣ አስተዳደርና የሙስና መከላከል የአቅም ግንባታ ስልጠናዊ ውይይት አካሂዷል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር እሸቴ አስፋው መድረኩን ሲያጠቃልሉ እንደተናገሩት የአመለካከት ለውጥ ማምጣት የሁሉም መሠረት በመሆኑ ኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ተግባራትን ከማከናወን ባለፈ ሰፊ የሥነምግባር ግንባታ በማካሄድ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት እንደሚሠራ ገልጸዋል።

ም/ኮሚሽነሩ አክለውም ኮሚሽኑ የአቅም ግንባታ መድረኮችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል በመጠቆም በየዘርፉ የሚገኙ መከታተያ ክፍሎች ራሳቸውን በማጠናከር የተቋማቸውን አሰራር ከሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲከላከሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ ወዶ አጦ በበኩላቸው መድረኩ ሙስናን በመከላከል እና ሥነምግባርን በመገንባት ትውልድ የማነፅ፣ ሀገር የመታደግ አጀንዳ ያነገበ መሆኑን ገልፀው፥ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በጋራ በመቀናጀት ሙስና ሊሸከም የማይችል ትውልድ በመፍጠሩ ረገድ ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በመድረኩ ማጠቃለያ አስተያት የሰጡ ተሳታፊዎች እንደገለፁት በአራቱ ቀናት የተሠጠው የአቅም ግንባታ ስልጠና በቀጣይ በአለም ባንክ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ እንዲተገበሩ የተሻለ ክትትል ለማድረግ ተጨማሪ አቅም እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል።

በተጨማሪም ሥነምግባር በመላበስ የሌሎችንም ስነምግባር ለመገንባት እንደሚተጉ አሥተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በዘርፎች የተካሄደው የሙስና ስጋት ጥናት የተቋማት አመራሮች ውይይት አድርገውበት ወደ ተግባር መግባት እንደሚገባው አንስተዋል።

ባለፉት አራት ቀናት ስልጠናዊ ውይይቱ በዋናነት ያተኮረው በፕሮጀክት ግዥ አስተዳደር፣ በሥነምግባር፣ በፕሮጀክት አስተዳደር እና ሙስና መከላከል እንዲሁም የዘርፉ የሙስና ስጋት ጥናት፣ ሙስና መከላከል ስትራቴጂክ፣ የክትትል ሪፖርት እና የዘርፉ የፕሮጀክት ማረጋገጫ ሪፖርት ሰነድ ላይ ነበር።

የኮሚሽኑ አመራሮች ከተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም (UNDP Ethiopia) አመራሮች ጋር በቀጣይ በሚሰሩ ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሄዱ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች ከተባበሩት መንግስታት ልማት ፕሮግራም (UNDP Ethiopia) አመራሮች ጋር በቀጣይ የኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል እንዲጠናከር በትብብር የሚሰሩ ተግባራትን በጋራ በመወያየት መለየት ችለዋል።

በስልጤ ዞን ተቀጥረው ሲሰሩ የነበሩ 82 መምህራን የትምህርት ማስረጃ ሐሰተኛ መሆኑ ተገለፀ

በደቡብ ክልል ስልጤ ዞን የትምህርት ማስረጃ የማጣራት ስራ ተሰርቶ የ82 መምህራን የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑ ተረጋግጧል።

በዞኑ በሚገኙ በሁሉም የወረዳ ሴክተር መስሪያቤቶች ተቀጥረዉ በሚሰሩ አራት ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ሰራተኞች የትምህርት ማስረጃ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተልኮ እንዲጣራ በመደረጉ 67(ስልሳ ሰባት) መምህራን ተደናግጠዉ ስራቸዉን ጥለዉ መጥፋታቸዉ ተነግሯል። ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ አቅርበዉ ከተቀጠሩ 82 መምህራን ዉስጥ 28 (ሀያ ስምንት) መምህራንን ፖሊስ በቁጥጥር ስር አዉሎ ምርመራ አጣርቶባቸዋል።

ምርመራ ከተጣራባቸዉ 28 ተከሳሾች ዉስጥ ፍርድ ቤት ቀርበዉ የተቀጡት 13 ተከሳሾች ናቸው። የተቀሩት በፍርድቤት በዋስ ከተለቀቁ በኋላ አካባቢያቸዉን ጥለዉ የተሰወሩ ሲሆን፥ ፖሊስ ተከሳሾችን አድኖ በመያዝ ለፍርድ ለማቅረብ ብርቱ ክትትል እያደረገ እንደሚገኝ የደቡብ ፖሊስ በፌስቡክ ገፁ አጋርቷል። በመንግስት እና በግል ህዝባዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚሰሩ ሰራተኞች የትምህርት ማስረጃቸዉ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ስራ በሁሉም አካባቢዎች ተግባራዊ በማድረግ ሀገርና ህዝብን መታደግ ያስፈልጋል።

የገቢዉን ዘርፍ ዋንኛ ማነቆ የሆነውን ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ታሳቢ ያደረገ የስራ ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ ተገለፀ

በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሰራተኞች እና አመራሮች የገቢውን ዘርፍ ዋንኛ ማነቆ የሆነውን ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል እና አቅም ለመፍጠር ታሳቢ ያደረገ የስራ ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱ ተገለፀ። የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኩ የገቢው ዘርፍ ዋንኛ ማነቆ የሆነውን ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል እና አቅም ለመፍጠር ታስቦ መዘጋጀቱን ተገልጿል።

በግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኩ ላይ የታክስ እና የጉምሩክ አምባሳደር አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ አገራችን ኢትዮጵያ አንገቷን ቀና አድርጋ እንድትራመድ በገቢ ማሰባሰብ የተሰማራችሁ ባለሙያዎች በስነ-ምግባር እንድትሰሩ አገራችን አደራ ሰጣችኋለች ብለዋል። የገቢ ሰብሳቢ ባለሙያዎች ግብር ከፋዩ እንዳይጉላላ እና ጊዜውን በአግባቡ እንዲጠቀም፣ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በትጋት እና በስነ-ምግባር መታነጽ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ያሬድ ፍቃደ በበኩላቸው የስነ-ምግባር ጉዳይ የቅድሚያ ቅድሚያ ተሰጥቶ በየወሩ የሚሰራበት ትልቅ አጀንዳ እንደሆነ መግለጻቸውን ከገቢዎች ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ አመላክቷል።

በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ ሲካሄድ የነበረው የጥያቄና መልስ ውድድር የማጠቃለያ ፕሮግራም ተካሄደ

የፌደራል የስነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬት ጋር በመተባበር ሲያካሂድ የነበረው የግንዛቤ ማስጨበጫ ጥያቄና መልስ ውድድር ተጠናቀቀ።

የውድድሩ ዓላማ ተወዳዳሪዎች የተሰጣቸውን ተግባራት በእውቀት እና ክህሎት መምራት እንዲችሉ፣ አቅማቸውን እንዲገነቡ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር እና ህብረተሰቡ በስነምግባር እና ፀረ-ሙስና ያለውን ግንዛቤ ለማጎልበት እንዲሁም ተደራሽ ለማድረግ ያለመ መሆኑን በማጠቃለያ ፕሮግራሙ ላይ ተብራርቷል።

ጥያቄና መልስ ውድድሩ ሙስናን ለመከላከል፣ ማህበረሰቡ ግንዛቤ የሚያገኝበትና ሙስናን በተግባር የሚታገልበት መሆኑን የውድድር ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪም ውድድሩ እኛ ተወዳዳሪዎች አቅም ያጎለበትንበትና የተለያዩ ሀሰቦችን የተጋራንበት በመሆኑ የወደፊት ስራችንን ተጋግዘን በጋራ ለመስራት ይረዳናል በማለት ገልፀዋል። የጥያቄና መልስ ውድድሩ በዋልታ ሚዲያ ኮርፖሬት በተከታታይ ፕሮግራሞች ለረጅም ጊዜ የቀረበ በመሆኑ፤ ህብረተሰቡን ለማስተማርና ለማሳዎቅ እንዲሁም ለማነቃቃት እና የጉዳዩ ባለቤት ለማድረግ የተሰራው ስራ ጠቃሚ ነው ብለዋል።

የጥያቄና መልስ ውድድሩ 560 ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በሁለት ዙር ተከፍሎ የተካሄደ ሲሆን የመጀመሪያው ዙር በ32 ቡድን 96 ተወዳዳሪዎች ተሳትፈዋል፤ በሁለተኛው ዙር ደግሞ በ16 ቡድን 39 ተወዳዳሪዎች ተሳትፈው ሰላም በሚባል ቡድን አሸናፊነት ውድድሩ ተጠናቋል።በመጨረሻም የኮሚሽኑ እና የዋልታ ሚዲያ ኮርፖሬት ኃላፊዎች በተገኙበት ለተሳታፊዎች የምስክር ወረቀት በመስጠት የማጠቃለያ ፕሮግራም ማካሄድ ተችሏል።

ታማኙ የባጃጅ ሹፌር ያገኘውን 27 ሺህ ብር ለባለቤቱ መለሰ

ወጣት አማን አሌ ይባላል፥ በሰሜን ሸዋ ዞን አጣዬ ከተማ ቀበሌ 03 መነሃሪያ አካባቢ ባጃጅ በማሽከርከር ህይወቱን ይመራል።

ከተሳፋሪዎቹ አንድ ደንበኛው 27,000 ብር ባጃጁ ላይ ጥለውት እንደወረዱ ያገኘና ገንዘቡን ለፖሊስ አሳውቆ የባለቤቱን መገኘት ሲጠባበቅ የቆዬ ሲሆን፥ የገንዘቡ ባለቤት አቶ ደበበ አይችሉህም የተባሉ ግለሰብ ገንዘቡን ከባንክ አውጥቶ ለግብይት ይዘውት እንደነበርና እንደጠፋባቸው ለፖሊስ በመግለፃቸው ከታማኙ የባጃጅ አሽከርካሪ ገንዘቡን መረከባቸውን መረዳት ችለናል።

የሙስናና የሥነ-ምግባር ጉድለቶችን ለማረም ከመንግሥት ተቋማት ባሻገር የቤተ-ዕምነቶች አበርክቶ ላቅ ያለ በመሆኑ ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል- አቶ ጃንጥራር ዓባይ

የሙስናና የሥነ-ምግባር ጉድለቶችን ለማረም ከመንግሥት ተቋማት ባሻገር የቤተ-ዕምነቶች አበርክቶ ላቅ ያለ በመሆኑ ሁሉም ኃላፊነቱን እንዲወጣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የስራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ ጥሪ አቀረቡ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከአዲስ አበባ የሐይማኖት ተቋማት ጉባዔ ጋር በመተባበር ስለ ሙስናና ብልሹ አሰራር ምንነት፣ የሌሎች አገራት ተሞክሮ፣ እንደ አገር ያለው አስቻይ ሁኔታ እና ከቤተ-ዕምነቶች ምን ይጠበቃል በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ተደርጓል።

በውይይቱ መግቢያ የተገኙት አቶ ጃንጥራር ዓባይ፥ እንደ ከተማ ዘርፈ-ብዙ የልማት ስራዎች ቢኖሩም፥ እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎችን ግን ከማኅበረሰቡ ጋር በመወያየት እያለፍን እንገኛለን ማለታቸውን አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ ዘግቧል።

ከፈተናዎቹ ውስጥ ሌብነትና ብልሹ አሰራር ዋነኛው መሆኑን ያነሱት ምክትል ከንቲባው በማኅበረሰብ ግንባታ ውስጥ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ገንብቶ ማጠናቀቅ የሚቻለውም የእድገት እንቅፋት የሆኑ ብልሹ አሠራሮችና ሌብነትን የዕምነት አባቶች እያወገዙ መሄድ ሲቻልም ነው ብለዋል።

በክልሉ በዓለም ባንክ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሠራር በጸዳ መልኩ ተተግብረው ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ የተጠናከረ ክትትል ይደረጋል - ኮሚሽነር መንግስቱ ላሎ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በዓለም ባንክ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሠራር በጸዳ መልኩ ተተግብረው ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ የተጠናከረ ክትትል እንደሚደረግ የክልሉ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር መንግስቱ ላሎ ገለጹ።

ኮሚሽኑ የሚመለከታቸው ተቋማት ኃላፊዎች፣ የክልል ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች እና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በጉዳዩ ዙሪያ ያተኮረ የምክክር መድረክ አካሂዷል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሥነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር መንግሥቱ ላሎ በመድረኩ እንደገለጹት፥ የኢትዮጵያ መንግስት ከዓለም ባንክ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በጤና፣ በትምህርት፣ በግብርና፣ በውኃና ኢነርጂ፣ በፋይናንስ፣ በሥራ ዕድል ፈጠራና በከተማ መሠረተ-ልማት ዘርፎችን ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶች በመተግበር ላይ ናቸው።

ኮሚሽኑ በአለም ባንክ ትብብር በክልሉ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በጸዳ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆኑ የክትትል ስራ እየተከወነ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ ቀደም በተካሄዱ የክትትል ሥራዎች በፕሮጀክቶቹ አተገባበር ላይ የጥራትና በተያዘላቸው

ጊዜ ያለመጠናቀቅ ክፍተቶችን ጨምሮ በሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር ያነሰ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በክልሉ በዓለም ባንክ ትብብር በሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በማረም ከሙስናና ብልሹ አሠራር በጸዳ መልኩ ተተግብረው ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ኮሚሽኑ የጀመረውን የክትትል ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ኮሚሽነር መንግስቱ ተናግረዋል። በቅርቡ በተሻሻለው የኮሚሽኑ አዋጅ መሠረት ክትትል በማድረግ የሚገኙ ግኝቶችን መሠረት ያደረገ ተጠያቂነትን ለማስፈን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነቱን ይወጣልም ብለዋል።

በአለም ባንክ ትብብር የሚተገበሩ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ጥራትና ውጤታማነት ለማሣደግ ህብረተሰቡን በባለቤትነት ያሣተፈ ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅ ጠቁመው፥ ባለድርሻ ተቋማት በተቀናጀ መንገድ እንዲሰሩም ጥሪ አቅርበዋል። ፕሮጀክቶቹን በሚተገብሩ ተቋማት የሚገኙ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይገባል ብለዋል።

የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ አቶ ዚያድ አብዱላዚ በበኩላቸው፥ በዓለም ባንክ ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በትክክል ካልተተገበሩ የሚያደርሱት ጉዳት ዘርፈ-ብዙ መሆኑን ገልጸዋል። ለህዝብ ጥቅም ሲባል የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመው፥ የክልሉ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጀመረውን የቁጥጥር ሥራ በተቀናጀ መልኩ ማስቀጠል አስፈላጊ መሆኑን መግለፃቸውን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዘግቧል። በዓለም ባንክ በሚገኝ ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን የሚያስፈጽሙ ተቋማትም በገቡት ውል መሠረት የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የመከታተል ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

www.feacc.gov.et | www.facebook.com/feaccOfficial | t.me/feacc

ኮሚሽኑ ለእቅድ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጠ

የፌደራል የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለክልል እና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የእቅድ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ከፕላን እና ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጠ።

ስልጠናው በዋናነት የእቅድ ምንነትና አዘገጃጀት፣ የእቅድ ክትትልና የሪፖርት አቀራረብ እና የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) እቅድ ዝግጅት ዙሪያ እንዲሁም የ2015 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ክትትልና ድጋፍ ላይ ያተኮረ ነው። በተመሳሳይ ዜና ኮሚሽኑ ለዘርፉ የህዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ኃላፊዎች እንዲሁም ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መድረክ አካሂዷል።

በተመሳሳይ መረጃ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ለክልል እና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለኮሙኒኬሽን ኃላፊዎች እንዲሁም ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጥቷል።

የሥልጠና መድረኩ በዋናነት በዲጂታል ኮሙኒኬሽን አሠራር፣ ማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም እንዲሁም በቀጣይ በቅንጂት ስለሚሠሩ ተግባራት ላይ ያተኮረ ነበር።

የኮሚሽኑ አመራር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን (UNCAC) አፈጻጸም ላይ በተካሄደ ስብሰባ ተካፈሉ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸረ-ሙስና ኮንቬንሽን (UNCAC) አፈጻጸም ላይ ያተኮረ 14ኛ የ Inter Governmental Review (IRG) ስብሰባ በቬይና አስትሪያ ተካሂዷል። በዚህ ስብሰባ ሀገራችን ኢትዮጵያ በኮሚሽኑ የስነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ ወዶ አጦ አማካኝነት ተሳትፋለች።

በመድረኩ ላይም የሀገራችን አጠቃላይ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴን በተመለከተ በም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ ገለጻ ከማቅረብ ባሻገር ከሌሎች ከሀገራት የፀረ-ሙስና ትግል ልምድ መውሰድ ተችሏል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀረ-ሙስና ኮንቬሽን (UNCAC) አፈፃጸም የውይይት መድረኩ ከሰኔ 05 - 09/10/2015 ዓ.ም ለአምስት ተከታታይ ቀናት ተካሂዷል።

ለአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ሴት ጋዜጠኞች የሥነምግባርና ግብረገብ ስልጠና ተሰጠ

የአብክመ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በክልሉ ውስጥ የሚታዩ የሥነምግባር ስብራቶችን ለማስተካከል በተለያዩ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ለሚገኙ ሰራተኞች የሥነምግባርና ግብረገብ ስልጠና መሰጠቱ ተገለፀ።

የስነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስልጠና ባለሙያ አቶ ዘላለም ንጉሴ በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ድርጅት በመገኘት ለድርጅቱ ሴት ጋዜጠኞች በአመለካከት፣ በስብዕና ምንነት፣ በስነምግባርና ግብረገብነት ዙሪያ፣ ስለአስተሳሰብ ደረጃ፣ እራስን ከመቆጣጠርና ትህትናን መላበስ እንዲሁም ቅድመ አያቶቻችን ምን ያክል በአስተሳሰብ የላቁ፣ በእውቀት የመጠቁ እና በክህሎት የረቀቁ መሆኑን ከአሁኑ ትውልድ ጋር በማወዳደር ሰፋ ያለ ስልጠና መስጠት ችለዋል።

የምዕራቡ ዓለም ባህል ወደ ሀገራችን በተለያዩ ምክንያቶች ሰርገው በመግባት ብዙ ነገራችን ላይ ትልቅ ተፅዕኖ እያሳደሩ ነው፣ በመሆኑም ሴቶች ከሁሉም በላይ ለልጆቻቸው ቅርብ በመሆናቸውና ያለውን የፀባይ ለውጥ በቀላሉ መረዳት ስለሚችሉ፣ የደረሰብንን የሥነምግባር ስብራቶች ለመከላከል ባላቸው አቅም ሁሉ ሊታገሉ እና ለልጆቻቸው ዘብ ሊቆሙ ይገባል በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አቶ ዘላለም በኮሚሽኑ ድጋፍና በባለሙያዎች የተቋቋመ ኢትዮጵያዊ የሥነምግባርና የግብረገብ ማህበር በመኖሩ፣ ትውልዱ እየሄደበት ያለውን የተሳሳተ ኢ-ሥነምግባራዊ አቅጣጫ ለመመለስ የማህበሩ አባል በመሆን የጋራ ትግል ማድረግ ይቻላል በማለት መልክታቸውን አስተላልፈዋል።

ተሳታፊዎች በበኩላቸው ኮሚሽኑ እየሰጠው ያለው የግንዛቤ ፈጠራ ስራ እጅግ የሚደነቅና መቀጠል ያለበት ተግባር ነው፤ ሴቶች ብቻ ሳንሆን ሁሉም የድርጅቱ ሰራተኞች መሰልጠን ቢችሉ የተሻለ የጋራ ግንዛቤ በመያዝ በየቤታችን ያለውን ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊት ሁሉ መታገል ይቻላል ማለታቸውን የአማራ ክልል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በፌስቡክ ገፁ አጋርቷል።

የስልጠናው ተሳታፊዎች ስልጠናው ባለፉት ጊዚያት ምንም ትኩረት አልተሰጠውም፤ ነገር ግን ችግሩ በእየቤታችን ሁሉ ያለ መሆኑን ግልፅ አድርጎ ያሳየን በመሆኑ፣ ቀጣይ ለልጆቻችን፣ ለአካባቢያችንና ለክልላችን ህብረተሰብ ባለን ሙያ ሁሉ በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ የማንቃት፣ ከባህላችንና ከልማዳችን ያፈነገጡ ድርጊቶችን ሁሉ የማውገዝ እና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራት እንችላለን በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል።

የሙስና መረጃ ትንተና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጠ

የፌደራል የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለፌደራል የመንግስት ተቋማት የስነምግባር መኮታተያ ክፍል የሙስና መረጃ ትንተና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መድረክ አካሄደ።

ስልጠናው በዋናነት ከተለያዩ ምንጮች የሙስና መረጃ አቀባበል፣ የሙስና መረጃ ትንተና፣ አያያዝና ክትትል፣ የሙስና ወንጀል ምንነት፣ ልዩ ባህሪያትና ደረጃዎቹ እንዲሁም የህዝብ አስተያየት መቀበያ ስርዓት/የፐብሊክ ፊድባክ አፕሊኬሽን/ (https://epfs.gov.et) ለሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ ላይ ያተኮረ ነበር።

የሲዳማ ክልል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለፍትህ ተቋማት የአስልጣኞች ሥልጠና ሰጠ

የሲዳማ ክልል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለፍትህ ተቋማት አመራርና ሠራተኞች የአስልጣኞች ሥልጠና በይርጋለም ከተማ መስጠቱ ተገለፀ።

ሥልጠናው በዋናነት በሙስና ወንጀል ምንነት፣ ልዩ ባሕሪ እና መከላኪያ ስልት፣ የሙስና ወንጀል ምርመራ ስልት እና ልዩ የፀረ-ሙስና የማስረጃና ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ላይ ያተኮሩ መሆኑን የሲዳማ ክልል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በፌስቡክ ገፁ አጋርቷል።

ሥልጠናው ለሁለት ቀናት የሚቆይ ሲሆን፣ በሥልጠናው ላይ የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ የሙስና ወንጀሎች ክስ ዳይሬክቶሬት ዐቃቢያነ-ሕጎች፣ የሀዋሳና አከባቢ ዐቃቤ-ሕግ መምሪያ የሙስና ወንጀሎች ክስ ዐቃቢያነ-ሕጎች፣ የበንሳ አከባቢ ዐቃቤ-ሕግ መምሪያ የሙስና ወንጀሎች ክስ ዐቃቢያነ-ሕጎች፣ የክልሉ እና የሀዋሳ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን የሙስና ወንጀሎች መርማሪ ፖሊሶች እንዲሁም ከተቋማቱ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የተወጣጡ ሰልጣኞች ተሳትፈዋል።

ፀረ-ሙስና

በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
www.feaccdars.gov.et

ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

ርዕሰ -አንቀፅ

ለፀረ-ሙስና ትግሉ ውጤታማነት የሁሉም ማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው!

በፀረ-ሙስና ትግሉ ውጤታማ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች መካከል መላው ህዝቡ በትግሉ ውስጥ የሚያደርገው ተሳትፎ አንዱና ዋነኛው ነው። ይህ የህዝብ ተሳትፎ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ውስጥ በጥቂት የፀረ-ሙስና ተቋማት የሚከናወኑ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎች የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አይችሉም። የአገራችንም ሆነ የሌሎች አገራት ተሞክሮዎች ይህንን በግልፅ የሚያረጋግጡ ናቸው።

እውነታው ይህንን የሚያመላክት ቢሆንም፣ የፀረ-ሙስና ትግሉ ዋነኛ ባለቤቶች የፀረ-ሙስና ተቋማት ብቻ እንደሆኑ የሚገነዘበው የኅብረተሰብ ክፍል ትንሽ አይደለም። በመሆኑም ይህንን አስተሳሰብ ከመቀየር አንስቶ ኅብረተሰቡ በፀረ-ሙስና ትግሉ የሚኖረውን ተግባራዊ ምላሽ ማረጋገጥ ከፍተኛ ትኩረትን እና ጥረትን የሚጠይቅ ነው።

ኅብረተሰቡ ህፃናትን እና ወጣቶችን በሥነምግባር ኮትኩቶ በማሳደግ፣ ከሙስኞች ጋር በማንኛውም ሁኔታ ባለመተባበር፣ ሙስናን በመታገል ቁርጠኛ የሆኑና ይህንንም በተግባር ለማሳየት ለሚጥሩ ዜጎች እውቅና በመስጠት እና በማበረታታት፣ በሙስና ለመበልፀግ የሚጥሩትን በማጋለጥ፣ በመታገል እና በመኮነን እንዲሁም በሌሎችም መንገዶች ለፀረ-ሙስና ትግሉ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል።

በፀረ-ሙስና ትግሉ ዙሪያ ስለሚደረጉ ተሳትፎዎች ስናነሳ ሁሉም ዜጋ ተሳትፎውን ለማሳየት የሚችልበት ኢጋጣሚ መኖሩን መረዳት ተገቢ ነው። ከዚህ አንፃር በትግሉ ውስጥ ድርሻ የለኝም ብሎ ማሰብ ስህተት ይሆናል። በመሆኑም ሁሉም በአካባቢው የሚታዩትን የሥነምግባር ጥሰቶችም ሆነ የሙስና ድርጊቶችን በንቃት በመከታተል በተለያዩ አግባቦች ሊታገላቸው ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ የመንግሥት መስሪያ ቤት እና የልማት ድርጅት የእራሱን የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ የማድረግ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባት በፀረ-ሙስና ትግሉ ውስጥ ተሳትፎን ከማረጋገጥ እንዲሁም ፖለቲካዊ እና ሕጋዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት ባሻገር ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል። በአሁኑ ጊዜ አገራችን የገጠማትን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በወሳኝ መልኩ ለመቅረፍ እያንዳንዱ ተቋም ይህን ማድረጉ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በዚህ ረገድ የፍትህ አካላት ድርሻ የጎላ ነው።

ለመልካም አስተዳደር ችግሮች መቀረፍ የእያንዳንዱ የመንግሥት ተቋማት እና የፍትህ አካላት ድርሻ ቀላል የማይባል መሆኑን በመገንዘብ ተቋማቱ በዚህ ረገድ የሚያሳዩትን ተሳትፎ በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

በሕዝብ የገንዘብ መዋጮ የተቋቋሙ የግል ንግድ ተቋማት (Private Companies) እንደ የተቋማቱ ባህሪ ተፈፃሚ የሚሆን የፀረ-ሙስና ስትራቴጂ በመንደፍ የሚመሯቸውን ተቋማት ከሙስና እና ብልሹ አሠራር የፀዳ አገልግሎት መስጠታቸውን በሕዝብ እና በተገልጋይ ምስክርነት ማረጋገጥ ይገባቸዋል።

በመሆኑም በእነዚህ እና በሌሎችም አግባቦች በፀረ-ሙስና ትግሉ የሚኖሩ ተሳትፎዎችን በማረጋገጥ ትግሉን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ማሸጋገር የሁላችንም ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል።

ቆይታ

“እኛ መጡልን እንጂ መጡብን እንድንባል አንፈልግም!”

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ክብርት ወ/ሮ መሰረት ዳምጤ

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ባሳለፍነው በጀት አመት የኦዲተር መስሪያ ቤቱ የመልካም አስተዳደር ችግር የሆኑ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ያደረገው እንቅስቃሴ ምን ይመስል ነበር?

ወ/ሮ መሰረት ዳምጤ፡- ከተልዕኳችን አንጻር እኛ የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ውስጣዊም፣ ውጫዊም ናቸው። እንደሌላው መስሪያ ቤት ስራ የምንጀምረው ሐምሌ ወር ላይ አይደለም። የኡዲት ስራ በመጋቢት ፣ ተጀምሮ ጥር 30 ላይ ነው የሚጠናቀቀው። ከዚያ በፊት በተቋማችን የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርተዋል። ስምሪት ከወሰዱ በኋላ ኡዲት ከሚደረጉ ተቋማት ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል የሚለውን የስነምግባር ዳሰሳ ሰርተናል። ከኡዲት ስነምግባር እና ውጤታማነት ጋር በተያያዘ መጠይቅ ተዘጋጅቶ መረጃዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ተወያይተን የዚህ በጀት አመት የእቅዳችን አካል አድርገናል። በዚሁ መረጃ እና ከሌሎች አካላት በተገኙ መረጃዎች 10 ኡዲተሮች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ወስደናል።

በተጨማሪም ስራውን ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ለመምራት ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በመጣ አዲስ አቅጣጫ መሰረት የተቋማችን የውስጥ ኡዲተር፣ የህግ ክፍል፣ የተቋማዊ ለውጥ እና የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በቅንጅት የሚሰሩበት አግባብ ለመፍጠር በአሁኑ ሰዓት ስልጠና በመውሰድ ላይ ናቸው። ከውስጥ አሰራር አንፃር እስካሁን ያነሳኋቸውን ስራዎች እያከናወንን ነው።

ከውጭ ስራዎች አንፃር ደግሞ የተቋማችን ዋና ተልዕኮ መንግስት የመደበውን በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ ነው። ይህ ደግሞ መልካም አስተዳደርን በማስፈን በኩል የራሱ አስተዋጽኦ አለው። በዚሁ መሠረት ከሚሰሩ ስራዎች መካከል አንዱ የፋይኔሺያል ኡዲት ሲሆን፣ በዚህም የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያዘጋጇቸው የሂሳብ መግለጫዎች ስህተት የሌላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፣ የመስሪያ ቤቶቹ የገቢ፣ የወጪ፣ የንብረት እና የሰው ኃይል አስተዳደር በመንግስት ደንብና መመሪያ መሠረት መከናወኑን እንመረምራለን እንዲሁም በክዋኔ ኡዲት የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶች እና ፕሮግራሞች እንዲሁም ፕሮጀክቶች ሥራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚከናወኑ መሆኑን እናረጋግጣለን። ይህ አጠቃላይ ህጋዊ የሀብት አጠቃቀም በተቋማት እንዲኖር እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ያግዛል። በተጨማሪም የልዩ ኡዲት ከፌዴራል ፖሊስ፣ ፍርድ ቤት፣ ፍትህ ሚኒስቴር እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመሆን ተጠያቂነት እንዲሰፍን እንሠራለን። ሌላው ከዝግጁነት አንጻር ፓርላማው አቅሙን እንዲያሳድግ ለማድረግ ከእኛ መስሪያ ቤት፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ከሚሽን፣ ከመንግስት ግዢና ንብረት ባለሥልጣን፣ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር በተውጣጡ ባለሙያዎች ለዋና እና ምክትል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት ተችሏል። ከዝግጅት አንጻር ይሄን ስራ መስራት ችለናል።

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በኡዲት ግኝቶች ላይ ተመስርቶ እየተወሰደ ያለ የእርምት እርምጃ እንዴት ይገለጻል?

ወ/ሮ መሰረት ዳምጤ፡- የፌዴራል ዋና ኡዲተር ዋና ስራው የኡዲት ሪፖርቶችን ለፓርላማ ማቅረብ ነው። ዋና ስራችን ግብዓት መስጠት ነው። ከዚሁ ጎን ለጎን የማስተማር ስራዎች እናከናውናለን። የኡዲት ሪፖርት ከላከን በኋላ ተቋማት የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅተው ይልካሉ። በዚያ መሰረት ክትትል እናደርጋለን። ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸውን እና የከዋኔ ኡዲት የተሰራባቸውን ኡዲት ሪፖርቶች ለመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንልካለን። እኛ በአስረጂነት፣ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲሁም ሌሎች በባለድርሻ አካልነት በአባልነት የምንሳተፍበት የጋራ መድረክ አለ። በዚህ መድረክ የኡዲት ሪፖርቶቹን መነሻ በማድረግ ወቅታዊ አቅጣጫ በቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አማካኝነት ይሰጣል። አስካሁን በታዩት ክፍተቶች መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር በ14 የመንግሰት ተቋማት የበላይ አመራሮች እና የፋይናንስ ሥራ ኃላፊዎች ላይ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም የገንዘብ ቅጣት አሳልፏል።

ሌላው ደግሞ የፍትህ ሚኒስቴርም በአስተዳደራዊ የሚጠየቁትን ይጠይቃል፥ በወንጀል የሚጠየቁትና ልዩ ኡዲት የሚፈልጉትን ድጋሜ እንዲሰራ እየጠየቀ በአጥፊዎች ላይ እርምጃዎች የሚወሰዱበት አሰራር አለ። ይህ ጥሩ እርምጃ ነው። በቀጣይ ተጠናክሮ ከሄደ የተሻለ ለውጥ ይመጣል ብለን እናስባለን። ከፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር የክትትልና የቁጥጥር ስራ እንዲሠራ አቅጣጫ ይሰጠዋል። ከተገኙ የኡዲት ግኝቶች መካከል ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ከታዩ ደግሞ ለፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲያያቸው ይደረጋል። በአጠቃላይ እነዚህ አሰራሮች ጥሩ ጅምሮች ናቸው። ተጠናክረው ሊቀጥሉም ይገባል።

በሌላ በኩል በእኔ አመለካከት ከኡዲት ተደራጊዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት አለ። እንደድሮው ምን ያመጣሉ የሚል አመለካከት የለም። ለእያንዳንዱ ነገር ንቁ ናቸው። በተለይ በዘንድሮው አመት በፓርላማው በኩል እና በተለያዩ የማህበራዊ የሚዲያ አማራጮች የኡዲት ሪፖርት በቀጥታ ለህዝብ ተደራሽ እየተደረገ መምጣቱ ግንዛቤውም በዚያው ልክ እንዲያድግ አድርጓል።

ተቋማትም ወደዚህ ችግር ላለመግባት ጥረት ያደርጋሉ። አሁን አሁን ተቋማት ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያደርጉት ሂደት ከበፊቱ በጣም የተሻለ ነው። ወደፊት ግንዛቤ ወስደው በንቃት ከሰሩ ከዚህ የተሻለ ውጤት ይመጣል ብለን እናስባለን።

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ተቋሙ ከፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እንዴት ይገለጻል? በቅርቡ በጋራ ለመስራት የተፈራረማችሁባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

ወ/ሮ መሰረት፡- ጉዳዩ አሁን የተጀመረ አይደለም። ከዚህ በፊትም ሁለቱ ተቋማት በጋራ ተቀናጅተው ሲሰሩ የቆዩ ቢሆንም ከስምምነት ያለፈ በዚህ ጊዜ እንገናኛለን፤ በዚህ ግዜ እንሰራለን የሚል ቅንጅታዊ የአሠራር ሥርዓት ዘርግተው አልነበረም። የአሁኑ ስምምነት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ይበልጥ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ነው። እንደሚታወቀው ሙስና ውስብስብ ነው፣ አሳሳቢም ነው። በየጊዜው ከቴክኖሎጂ ጋር መልኩን እየለዋወጠ ይሄዳል፣ የአለም መንግስታትንም ሁሉ ያሳሰበ ጉዳይ ነው።

በዚህ የተነሳ የአለም አቀፍ የኡዲት ተቋማት ማህበር (INCOSAI) 23ኛውን የዋና ኡዲተሮች ጉባኤ በራሺያ ባካሄደበት ወቅት የዋና ኡዲተር መስሪያ ቤቶች ከፀረ-ሙስና ተቋማት ጋር በትብብር መስራት እንዳለባቸውና ለዚህም የሚረዳ ሰነድ እንዲዘጋጅ አቅጣጫ አስቀምጦ ነበር። ይህን ተከትሎ የዋና ኡዲተር መ/ቤቶች ከፀረ-ሙስና ተቋማት ጋር በጋራ እንዲሠሩ የሚያስችላቸው ሰነድ ማህበሩ በወከላቸው አካላት ተዘጋጅቶ በ24ኛው ዓለም አቀፍ የኡዲት ተቋማት ጉባኤ (INCOSAI) ቀርቧል።

እኛም ይህንን ሰነድ በመቀበል በሀገራች ካለው የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር ሰነዱ በጋራ ተፈጻሚ በሚሆንበት አግባብ ስንሰራ ቆይተናል። ምክንያቱም የኡዲት ተቋማት ብቻቸውን ትርጉም ያለው ስራ መስራት አይችሉም። በጋራ ብንሰራ ውጤታማ እንሆናለን የሚል መነሻ ሃሳብ ስለነበረ ነው። እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ አጣጥመን መስራት ይኖርብናል። ከዚህ ተነስተን እኛ ምንድን ነው መስራት ያለብን ብለን ሰነዱ በእኛም ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም ሲታይ ከቆየ በኋላ የሁለትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት አዘጋጅተን ተፈራርመናል።

እንደኛ ካሉ ተቋማት ጋር በጋራ ብንሰራ ልንከላከላቸው የምንችላቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ሌላው በሁለታችንም ያለው ተልዕኮ ተመሳሳይነት ያለው ነው። ከሚሽኑ ስነምግባርን በመገንባት ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ ያለው ሲሆን፣ የእኛ ተቋም ደግሞ የመንግስት በጀት በህግና ደንብ መሰረት መከናወኑን አረጋግጦ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የበኩሉን ሚና የሚጫወት ነው።

ከዚህ አንጻር ከተሰጠን ተልዕኮ በተጨማሪ በጋራ ብንሰራ የተሻለ ውጤት እናመጣለን የሚል እሳቤ ስላለ ነው። በጋራ ከምንሰራቸው መካከል አንዱ የመረጃ ልውውጥ ነው። የፌዴራል ዋና ኡዲተር መስሪያቤቱ ባህሪው የተነሳ መረጃዎችን ያመነጫል። በተለይ ከወንጀል እና ከሙስና ጋር የሚያያዙ ጉዳዮችን ለፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቅረብ ተጨማሪ ጥናት ተደርጎ እርምጃ እንዲወሰዱ የራሱ አስተዋጽኦ አለው። ሌላው የአቅም ግንባታ ስልጠና ነው። በሁለቱም ተቋማት የሚታዩ ክፍተቶች መሰረት በማድረግ ስልጠና እንሰጣለን። ከተልዕኳችን አንጻር በጋራ የግንዛቤ ስራዎችን እየተዲጋገፍን መሰጠት እንችላለን። ሌላው የመፍትሄ ሀሳቦችንም በጋራ እናጠናለን። ችግር መፈለግ ብቻ ሳይሆን የመፍትሄ ሃሳቦችንም በጋራ ለማየት ነው ያሰብነው። ከዚሁ በመነሳት የተሻለ አፈጻፀም ያላቸውን ተቋማት በመለየት ደግም እርስ በእርስ ልምድ እንዲለዋወጡ የማድረግ ሥራ ይሠራል።

በተጨማሪ የትግበራ እቅድ ማውጣት ይኖርብናል። በየሁለት ወሩ እየገመገምን ውጤቱን እንዳስፈላጊነቱ በሚዲያ በጋዜጣዊ መግለጫ አመቺ በሆነ መልኩ ተደራሽ እናደርጋለን። በሁለቱም ተቋማት በኩል ሊሰሩ የሚችሉ ባለሙያዎችን መመደብ እንዳለብን ተስማምተናል። በዚሁ መሰረት በጋራ መስራት ከቻልን ጥሩ ውጤት እናመጣለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ለወደፊት በመስሪያ ቤቱ ውጤታማ የሙስና መከላከል ለማካሄድ የተቀመጠ ስትራቴጂ አሰራር ይኖር ይሆን?

ወ/ሮ መሰረት፡- በነገራችን ላይ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባስቀመጠው አሰራር መሰረት ከተቋሙ የስራ ባህሪ አንጻር የተቃኘ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ አቅድ አለ። እሱን ነው እየመነዘርን ወደ ተግባር እየገባን ያለነው። ስትራቴጂው ሲጠና መከታተያ ክፍል አልነበርም፤ ከዚያ በኋላ ክፍሉን አደራጅተናል። አሁንም በሳይንስ የተደገፈ አሰራር ለመተግበር በአሁን ወቅት ስልጠና እየተከታተሉ ያሉ ባለሙያዎች ያሉን ሲሆን፣ የተሻለ አሰራር ይዘው ያመጣሉ ብለን እንጠብቃለን። ስለሆነም በየጊዜው ወቅቱን የሚመጥን አሰራር እየፈተሸን እንሄዳለን።

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ተቋማችሁ የመልካም አስተዳደር ችግር የሆኑ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል በሚያደርገው ጥረት ከህዝብ ምን ይጠበቃል?

ወ/ሮ መሰረት፡- ይህንን ጥያቄ የምወስደው ኡዲት ከምናደርጋቸው ተቋማት አንጻር ነው። እኛ ኡዲት ከምናደርጋቸው ተቋማት መካከል ቀና አመለካከት ያላቸው እና የሚያግዙን አሉ። እኛ መጡልን እንጂ መጡብን እንድንባል አንፈልግም። ኡዲተር ኢጋዥ ነው የሚል አመለካከት እንዲኖር እንፈልጋለን። ኡዲት ገለልተኛ ሆኖ የሚሰራ ሙያዊ ተቋም ነው። ባለሙያዎችም ሙያቸውን እንጂ ሌላ ተልዕኮ የላቸውም። ከዚህ አንጻር የተቋማትን ቀና ትብብር እንፈልጋለን። ከትብብሩም ውስጥ ባለሙያዎቻችን ቢሮ ሲሄዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። ኡዲት በየዓመቱ የሚካሄድ በመሆኑ ቋሚ ቢሮ ያስፈልጋቸዋል።

በአንድ ተቋም ቢያንስ ከሶስት እስከ ስድስት ወር የሚቆዩበት ጊዜ ስለሚኖር ቢሮ ከማመቻቸት አንጻር ትኩረት ማድረግ አለባቸው። ሌላው መረጃዎችን ከማደራጀትና ከማቅረብ አንጻር ድጋፍ ማድረግ አለባቸው። ሌሎች ደግሞ ኡዲተሮች የማይደርሱባቸው አሰራሮች ካሉ ጥቆማ ማድረግ አለባቸው። በመሆኑም ከተቋማት ይሄን ትብብር እንፈልጋለን። ምክንያቱም ያለመረጃ የኡዲት ሥራ ባዶ ነው። መረጃ ያስፈልገናል፤ የሰማነውን ሳይሆን በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት ስለምናመነጭ በዚያ ምክንያት ተቋማት ቀና ትብብር ማድረግ አለባቸው። ይህን በማድረግ በኩል መልካም ትብብር የሚያደርጉ እንዳሉ ሁሉ አንዳንድ ተቋማት ከፍተት ስላለባቸው ያንን እንዲያርሙ እንፈልጋለን።

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- እናመሰግናለን።

ሳይቃጠል በቅጠል

የተቋም አመራርና ሙስና መከላከል

በተስፋዬ ሻሜቦ

ሙስና በሥነምግባር ዝቅጠት፣ በአቋራጭ የመበልጸግ ፍላጎት/ተነሳሽነት ወይም በሰዎች ወይም በሁኔታዎች ግፊት/ተጽዕኖ ወይም ምቹ ሁኔታዎች/የቁጥጥር መላለት ሲገጥም ይሰራል። ይህን የሚሠሩት ደግሞ የመንግስት ሀብትና ንብረት ላይ የማዘዝ፣ የማስተዳደርና የመጠበቅ ኃላፊነትና ሥልጣን ያለቸውና የመሳሰሉ ሰዎች ናቸው። የሥነምግባር ዝቅጠት የሚመጣው ከተፈጥሮ የራስ ወዳድነት ወይም የስግብግብነት ባህርይ መያዝ እንደሆነም ይታወቃል።

የሰዎች ወይም የሁኔታዎች ግፊት ደግሞ አመራሩ ወይም ሠራተኛው የሚሠራበት ቦታና ያለውን ኃላፊነት ደረጃ የሚያውቁ ሰዎች አጋጣሚውን እንዲጠቀም ሲመክሩት ወይም ከቤተሰብ ግፊት ሲበዛበት ወይም የሚኖርበት የኑሮ ሁኔታ ከገቢው ጋር ሳይጣጣም ሲቀርበት ክፍተቱን ለመሙላት ሙስና ለመስራት ይነሳሰል፣ ይሠራል። ምቹ ሁኔታ የሚባለው የሚሠራበት መሥሪያ ቤት ውስጥ ሠነድ የማዘጋጀትና በሰነዶች ላይ የመወሰን ሥልጣን ከተሰጠው ወይም በሥራ ላይ ተገቢ የሆነ የክትትልና ቁጥጥር አለመኖሩን ሲያወቅ ወይም ለሥራው ቅልጥፍና የተዘጋጁት ህጎች ላይ የሚያስጠይቅበት ሁኔታ እንደሌለው ሲረዳ አጋጣሚውን በመጠቀም ሙስና ይሠራበታል።

በመሆኑም ተቋማትን እንዲመሩ የተሾሙ ወይም በሜሪት የተመደቡ የሥራ ኃላፊዎች በተቋም ውስጥ ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮችን በቅድሚያ በትክክል በመረዳት የመከላከል ግዴታ እንዳለባቸው ይታወቃል። ለዚህም ተቋሙ ምን ዓይነት ተልዕኮ እንዲያሳካ እንደተቋቋመ ከተቋሙ የማቋቋሚያ አዋጅ ላይ በትክክል በመረዳት ይህን ተልዕኮ በምን ያህል ደረጃ ለማሳካት እንደሚችሉ ርዕይ መንደፍ ይጠበቅባቸዋል።

ርዕይ ከተለመደው አነዳደፍ በተለይ በአፍሪካ እና በዓለም ተወዳዳሪነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን የዜጋውን ፍላጎት በማርካት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በሚያበቃ መልኩ የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል አጭርና ግልጽ እንዲሁም በጊዜ የተገደበ ርዕይ መንደፍ ያስፈልጋል።

ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተቋማት ርዕያቸውን ከአፍሪካ ወይም ከዓለም ተወዳዳሪ እንደሚሆኑ ይተንብያሉ እንጅ እንዴትና በምን ሁኔታ ተወዳድረው በደረጃ ላይ እንደሚቀመጡ ለራሳቸውን ግልጽ የሚሆን አይመስልም። ርዕይ ሲነደፍ ተልዕኮን ለማሳካት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ የት መድረስ እንዳለበት በጊዜ በመገደብ መቀመጥ እንዳለበት ይታወቃል።

ተልዕኮ ተቋማት ምንን ለማሳካት እንደተቋቋሙ በህግ ማዕቀፍ የሚደገፍ ስለሚሆን ይህን በትክክል በመረዳት ተልዕኮውን ማሳካት የሚያግዝ ርዕይ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። የተነደፈውን ርዕይ ለማሳካት የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች/ተኪታዮች ሊላበሱ የሚገቡ እሴቶችንና መርሆዎችንም ማስቀመጥ የግድ ነው። እሴቶችና መርሆዎች ርዕይን ለማሳካት የሚኬድበት መንገድ ላይ እያንዳንዱ የተቋሙ ተኪታይ ሥራ ኃላፊና ፈፃሚ ሊላበስና በትክክል ሊያውቀው ይገባል።

በአንዳንድ ተቋማት ውስጥ በተለምዶ ከአፍሪካና ከዓለም ግንባር ቀደም መሆን እየተባለ ርዕይ ይነደፋል። በርዕይ መሠረት ተቋሙ በምን ያህል ደረጃ ላይ ስለመገኘቱ ሳይታወቅ የርዕይ ዓመታት ያበቃሉ። አንዳንድ ደግሞ የተቋሙን ተልዕኮ በትክክል ባለመረዳት ከተቋሙ የሚጠበቀውን ብቻ አለመስራት ወይም የተቋሙ ያልሆኑ ሥራዎችን የመሥራት ሁኔታዎችም የሚታይ ነው።

የተቋሙ እሴቶችና መርሆዎች ተብለው የሚነደፉት በተቋሙ አመራርና ሠራተኞች በትክክል የማይታወቁና ለይስሙላ ብቻ ዕቅድ ሲታቀድ የሚገለጹ ወይም በተቋሙ በራፍ ላይ በታፔላ የሚለጠፉ ሲሆን፤

ከዋናው ነገር ርዕይ በምን ያህል እንደተሳካ የሚጠይቅ አካልም የለም።

በተቋሙ የተቀረጹ ርዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች በተቋማት ተኪታዮች (የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች) በትክክል የማይታወቁና በቂ ግንዛቤ ያልተያዘባቸው ስለሚሆኑ የሚነደፉ ግቦች የማይሳኩ ወይም በትክክል የማይተገበሩ ይሆናሉ። በሌላ በኩል ግቦቹ በተኪታዮች በቂ ተሳትፎ ባለመቀረጻቸው ምክንያት የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች የተቋሙን ርዕይና ተልዕኮ የሚያሳኩ ተግባራትን ለይተው በትክክል ግብ አቅዳው ከማከናወን ይልቅ አልባሌና ፋይዳቢስ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው ጊዜያቸውን ሲያባክኑ ሊዉሉ ይችላሉ። በተቋሙ ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ግቦችን በትክክል በመለየትና በደረጃ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ ለማሳካት ቅድሚያ ለሚሠጠው ሥራ በቂ በጀት በመመደብ ውጤታማ ለመሆን የሚደረግ ጥረትም እምብዛም ትኩረት የሚሰጥ አይደለም።

በመሆኑም በተቋም ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ የበጀት ወጪ የሚጠይቁ ሲሆኑ፤ አጋጣሚውን በመጠቀም በሆኑ ባልሆኑ ጉዳዮች የመንግስት በጀት ወጪ እንዲባክን ይደረጋል። የተቋሙ ርእይና ተልዕኮ የሚያሳኩ ግቦችን በመቅረጽና ቅድሚያ የሚሰጠውን በመለየት ለተቋሙ አመራርና ሠራተኞች በቂ ግንዛቤ በማሳደግና የባለቤትነት ስሜት በመፍጠር ወደ ተግባር የሚገባበት አክት ደካማ ስለሆነ ሌብነት ታቅዶ ይተገበራል። በተቋሙ ውስጥ ተልዕኮ ለማሳካት የሚረዱ ሻዥዎች በቅድሚያ የሥራ ክፍሎች ፍላጎትና የገበያ ዋጋ መረጃ ሳይያዝ ወደ ግዥ አፈፃፀም ስለሚኬድ አራቱም የግዥ ዑደቶች (የግዥ ዕቅድ፣ የዝግጅት ጊዜ፣ የጨረታ ግምገማ፣ የውል አስተዳደር፣) ሙስና መቼና እንዴት እንደሚሠራ የዲዛይን ሥራዎችን በመሥራትና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የታሰበውና የታቀደው ይፈፃማል። በተቋም ግዥ ከተፈቀደው በጀት 60 በመቶ በላይ ድርሻ ስላለው ታስቦበትና ታልሞ በተከፈተው ቀዳዳ የማይፈለጉና ጥራት የሌላቸውን ዕቃዎች በተጋነነ ዋጋ ግዥ በመፈጸም ሙስና ይፈፃማል።

በዚህ እሳቤ የተፈፀመው ግዥ ጥራት የሌላቸው ለአገልግሎት የማይፈለጉ ዕቃዎች ስለሚሆኑ ከተገዙ በኋላ ለፀሓይና ዝናብ እንዲጋለጡ ይደረጋል። አገልግሎቶች ሳይወዱ ክፍያ ይፈጸማል።

ተቋም የግንባታ ግዥ ካለው ደግሞ የአዋጭነት ጥናት ሳይደረግ፣ የገበያ ጥናት መረጃ ሳይያዝ፣ ለግንባታ ሥራ በቂ የካፒታል፣ የግንባታ መሳሪያዎችና የሰው ኃይል አቅም የሌለውን ተቋራጭ የጨረታው አሸናፊ በማድረግ ወይም የግንባታ ዝርዝር መግለጫና የዲዛይን ሥራን በተቋራጭ በማሠራትና በጨረታ በማወዳደር አሸናፊ በማድረግ ጥራት የሌለው ግንባታ በተጋነነ ዋጋ እንዲከናወን ይደረግና የመንግስት በጀት አላግባብ እንዲበክንና በሂደቱም የተወሰኑ ሰዎች በሙስና ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል።

የመንግስት ሀብትና ንብረቶች ስርቆት ነው። የመጀመሪያ በተቋም በጀት የተገዙና ለተቋም ተልዕኮ ማሳካት ተብለው የተገዙና በቀላሉ ሊሠረቁ የሚችሉ ሀብትና ንብረቶች በተቋሙ ርዕይና ተልዕኮ ላይ ግንዛቤ እንዲይዙና ባለቤትነት እንዲፈጠር ባልተደረጉ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሰርቀው ለግል ጥቅማቸው ሊያውሉ ይችላሉ። ምክንያቱ ደግሞ እነዚህ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ወደ ተቋም የሚመጡት የተቋሙን ርዕይና ተልዕኮ የሚሳያኩ ተግባራትን በማከናወን ራሴንና ሀገሬን ማሳደግ አለብኝ የሚለውን አመለካከት ይዘው ስለማይሆን ነው። በሌላ በኩል በተቋም ውስጥ በወር የሚከፈለውን ደመወዝ ብቻ አስበው ስለሚሠሩ የተቋም ሀብትና ንብረት እንዲሁም የህዝብ ሀብትና ንብረት የሚል የተቆርቋሪነት ስሜትም አይዙም።

ሌላው የመንግስት ሀብት የሆኑ ንብረቶችን በህገወጥ መንገድ በጉቦ ወይም በእከኝል ልከክህ መርህ በህገወጥ መንገድ ለግለሰቦች ተላልፎ የሚሰጡ፣ ከሥራ ቀን ውጪና በበዓላት ቀን የመንግስት ተሽከርካሪ ሠሌዳ በመለወጥ ጭምር በማከራየት ገቢ የሚያገኙ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ከጋራዥ ጋር በመመሳጠር ከፍተኛ ወጪ በማስወጣት የመንግስትን ሀብትና ንብረት የሚዘርፉ፣ የመንግስት መሬት ለህገወጥ ይዞታ ካርታና ግንባታ ፈቃድ በማዘጋጀት ለህገወጥ ሰዎች እንዲተላለፍ የሚያደርጉ፣ መብራትና ውሃ በህገወጥ መንገድ ያለቆጣሪ ለግለሰቦች የሚያስተላልፉ ወይም መብራትና ውሃ ለማስገባት ጉቦ የሚቀበሉ፣ መብራትና ውሃ የቆጠረውን እንዳይከፍል የሚያደርጉ፣ የህገሪቱ ፓስፖርት ለህገወጥ ተግባር እንዲውል የሚያደርጉ፣ ኬላ ላይ ጉቦ ተቀብለው የጦር መሳሪያ እንዲገባ የሚፈቅዱ፣ ነዳጅ በኮንትሮባንድ ወደ ውጪ ሀገር እንዲገባ የሚያደርጉ ወዘተ... ሰዎች ሙስና ይፈጽማሉ።

በተቋም አንዳንድ ሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የተቋሙን ዓላቂ ዕቃዎች ለተቋም ሥራ ሳይሆን ለግል ሥራ ይጠቀመበታል። ወረቀት፣ እስክርብቶ፣ ማስታወሻ ደብተር እና ቦርሳ ለራሳቸው ወይም ለልጆቻቸው ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጉታል።

ለሥራ አገልግሎት እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸውን ተሽከርካሪ በመንግስት በጀት ነዳጅ ሞልተው ለግል ጥቅም የሚያውሉት አሉ። ለሥራ የተፈቀደውን የመንግስት ተሽከርካሪ ከቤት ወደ መሥሪያ ቤት ወይም ከመሥሪያ ቤት ወደ ቤት የሚጠቀሙት የሥራ ኃላፊዎች ብዙ አይደሉም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የተቋሙን ተሽከርካሪ በመጠቀም የተቋሙን ርእይና ተልእኮ የሚያሳኩ ተግባራትን ለማከናወን ብቻ መጠቀም የሚል አመለካከት የሚይዙ የሥራ ኃላፊዎች ብዙ ናቸው ለማለት ያስቸግራል።

የአንዳንድ ሀገራት በተለይ ጃፓን ሀገር የመንግስት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለመንግስት ሥራ ሲሆን በመንግስት በጀት የተገዛውን እስክርብቶ ሲጠቀሙ፣ ለግል ጉዳይ ሲሆን ደግሞ በራሳቸው ገንዘብ የገዙትን እስክርቢቶ ይጠቀማሉ፣ ለዚህም ሁሌም ሁለት እስክርብቶ ይዘው ይጓዛሉ። በሀገራችን ተቋማት ውስጥ የሥራ ኃላፊ ከሆኑ ተሽከርካሪ መጠቀም ሙብቴ ነው ከማለት ውጭ ተሽከርካሪው የተቋም ስለሆነ የሚጠቀመው የተቋሙን ርእይና ተልዕኮ ለማሳካት የሚል አመለካከት የመያዝ አዝማሚያዎች በጣም እየተሸረሸ ስለሚገኝ ከተቋም ውጪ የሆኑ የግል ጉዳዮችን ለማስፈጸም እንደሚጠቀሙ በዚሁ ዙሪያ የተካሄደ አንድ ጥናት ሪፖርት ይገልፃል።

ለዚህ ማሳያ በመንግስት ተሽከርካሪ የግል ጉዳይ የማስፈጸም አዝማሚያዎች ስላሉ ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ መጠን እንዲኖር የማድረግ ሁኔታዎች መኖራቸው የሙስና ሥጋት እንዲፈጠር ምክንያት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።

የተቋም ራዕይና ተልዕኮ መቀረጽ ያለበት በተቋሙ የበላይ አመራር ነው። የበላይ አመራር ወደ ተቋም ሲመደብ መጀመሪያ ማድረግ ያለበት፣ የተቋሙን ራዕይ በትክክል መንደፍ ወይም የነበረውን ራእይና ተልዕኮ ለማሳካት መሥራት ነው።

በሀገራችን አዲስ አመራሮች ሲመደቡ አንዱ የነደፈውን ራእይና ተልዕኮ መቀየርና በአዲስ መተካት የመጀመሪያ ሥራቸው ነው። የበፊቱ አመራር የነደፈውን ራእይና ተልዕኮ መሳካት አለመሳካቱ ሳይረጋገጥ ሌላ ራዕይና ተልዕኮ ስለሚነደፍ ተቋሙ ምንም ውጤታማ ሳይሆን ርእይና ተልእኮ በመንደፍ ብቻ ዕድሜውን ያስቆጥራል እንጅ ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ተቋሙም የህዝብ ጥቅም በማስከበር እርካታና አመኔታ ሊያመጣ አይችልም።

ተቋም እንዲመራ የሚመደብ አመራር ሥነምግባር በመላበስ የሚመራ ከሆነ ተቋሙ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ሊቀንስ ይችላል። ሥነምግባር መላበስ ስንል መጀመሪያ ተኪታዮችን በትክክል ማወቅና አቅም መገንባት ነው። በሚመራው ተቋም ውስጥ ያሉት ተኪታዮች በተቋሙ ውስጥ በቆይታ ስለሚበልጡት ተቋሙ ምን ቢሠራ ውጤታማ እንደሚሆን ጠንቅቀው እንደሚያወቁ ይታወቃል። ስለሆነም አመራሩ የነደፈውን ርዕይ ለማሳካት በቅድሚያ የተኪታዮች ያላቸውን የአቅም ደረጃ ማወቅና ክፍተት ያለባቸውን መለየትና ለሥራ እንዲበቁ ማድረግም ይጠበቃል። ሌላው በሚያከናውናቸው፣ በሚወስናቸውና እርምጃ በሚወስድባቸው ጉዳዮች ፍትሃዊነትን የጠበቀ፣ ግልጽነትን የተከተለ፣ ተጠየቂነትን መርህ ያደረገ ከሆነ በተኪታዮች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኛል።

ለዚህም ለሥነምግባራዊ አመራር መርሆዎች ተብለው በምሁራን የተለዩት ፍትህዊነት፣ ሌሎችን ማክበር፣ አገልጋይነት፣ ታማኝነት፣ ለህዝብ ጥቅም መቆም የሚባሉ መርሆዎችን በመከተል ተቋሙን መምራት የግድ ነው። በተቋሙ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ሁሉምን ዜጎች በእኩል አይን ያለአድሎዎ እንዲስተናገዱ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ ዜጋው ከተኪታዮች የሚገጥሙትን እንግሎቶችና የእጅ መንሻ ጥያቄዎችን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚረዱ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ መተግባር ይጠበቃል። ለዚህም በተቋም ውስጥ ይህን ሥራ እንዲከታተሉ የቅሬታና አቤቱታ መቀበያ አሠራር መዘርጋት፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍልና የተቋማዊ የለውጥ ሥራ አመራር ክፍሎች እንዲሁም የኡዲት አገልግሎት ብቃትና ክሂሎት ባላቸው የሰው ኃይል የተደራጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የተደራጁ የሥራ ክፍሎች ደግሞ በተቋም አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ በተገልጋዮች ላይ የሚያገጥሙ እንግልቶችንና ሌሎች ችግሮችን ለመከላከል የሚያግዙ ዕቅዶችን በማቀድ እንዲተገብሩ የመከታተል፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በታዩት ችግሮች ላይ ወቅታዊና ዘላቂነት ያለው መፍትሄ የመስጠት ሥራዎች በተገቢ መልኩ መከናወናቸውን በጥንቃቄ ማረጋገጥ ይገባል።

ሌሎችን ማክበር ሲባል ተቋም ውስጥ እንደሀገሪቱ ከተለያዩ ማህበረሰብ የተወጣጡ አካላት ተመድበው ወይም ተቀጥረው ስለሚሠሩ ዜጎች በመሆናቸው

የተቋም አመራርና ... ወደ ገጽ 13 የዞረ

ሀገራዊ ምክክሩ ተሳታፊዎች ከተለያዩ ክልሎች የመጡ ሲሆን ከሁሉም ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጓል። በውይይቱ ወቅት ተሳታፊዎች ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ጠይቀዋል። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው።

ሀገራዊ ምክክሩ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው።

ሀገራዊ ምክክሩ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም ህብረተሰብ ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው።

ኮሚሽኑ ሀገራዊ ምክክሩ ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ ተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉ ተገቢ ነው።

የተቋም አመራርና ...

በትክክል መከበርና ማክበር አለባቸው። እንዲሁም ወደ ተቋማት አገልግሎት ሊወስዱ የሚመጡ የተለያዩ ማህበረሰብ አካላትን በተገቢ ማስተናገድ፣ ፍላጎታቸውን የሚያረካ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠትና በስብእናቸው ማክበር ያስፈልጋል።

አገልጋይነት ሲባል ለሌሎች ቅድሚያ የመስጠት ሥነምግባር ፅንሰ ሀሳብ ጥሩ ምሳሌ ነው። የአገልጋይነት ባህርይን የተላበሰ መሪ ለተከታዮቹ ደህንነትና ፍላጎት የሚጭነቅና ለዚህም አቅዶ የሚንቀሳቀስ ነው።

ታማኝነት ሲባል የአንድ ጥሩ መሪ ዋና መገለጫ ነው። አለመዋሸት፣ ለሌሎች ግልጽ መሆን፣ ነገሮችን ትክክለኛ ገጽታ ማሳየት፣ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትና እምነትን ማግኘት፣ የማይፈጽመውን ነገር ቃል አለመግባት፣ ግዴታዎችን አፍኖ አለማስቀረት፣ ተጠያቂነትን አለመሸሽ፣ ሰዎች የሚመኩበት ሰው መሆን እንዲሁም በተረጋጋ አመራር አመላከከትና ባህርይ ተከታዮችን ማክበርና ዜጋውን የሚያረካና ተጠቃሚ የሚያደርግ ተግባር ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ነው።

ለህዝቡ ጥቅም መቆም ሲባል አመራር ራሱንና የህብረተሰቡን ፍላጎቶችና ግቦች ለማሳካት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ተከታዮቹን ዓላማና ፍላጎት በማጤን፣ ለራስ ጥቅም ቅድሚያ የማይሰጥና ቅድሚያ ለህብረተሰብ አመለካከት ይዞ የሚንቀሳቀስ አመራር ማለት ነው።

የተቋም አመራር አገልግሎት የሚሰጡ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት ሂደት ላይ የተቋሙን መርሆዎችና እሴቶችን ተላብሰው አገልግሎት መስጠት ሲገባቸው መርሆዎችንና እሴቶችን የሚጣረሱ ተግባራት መፈጸማቸው ከተረጋገጠ ወቅታዊ የሆነ ተጠያቂነትን ማረጋገጥን ያስፈልጋል። እንዲሁም ተቋሙ ለሚሰጣቸው አገልግሎት ስታንዳርድ ማዘጋጀትና የተሰጡ አገልግሎት በስታንዳርዱ መሠረት ስለመሆናቸው መገምገምና በሚታዩት ልዩነቶች ላይ እርምጃ መውሰድ የአመራር ሥነምግባር መርህ የሚካተት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በሚሰጡት አገልግሎት ሥነምግባርንና ግብረገብነትን በመላበስ አገልግሎት የሚሠጡ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞችን ለይቶ ማበረታታትና ለሌሎች

በአርአያነት እንዲወሰድ ማድረግ ከተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚጠበቅ ነው።

በተቋም ውስጥ ግልጽነት እንዲሰፍን ማድረግ ከተቋም የበላይ አመራር የሚጠበቅ ግዴታ ነው። ተቋሙ ውስጥ ያሉ ህጎችና አሠራር መመሪያዎችን ወቅታዊነትን በመጠበቅ በሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በሚገባ እንዲታወቅና ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ፣ ተቋሙን የሚመለከቱ ማንኛውም ምስጥራዊ ያልሆኑ መረጃዎችን ትክክለኛና ተደራሽ የሆነ ሚዲያ በመጠቀም ለዜጎች ተደራሽ ማድረግ፣ ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎት ጥራት፣ ጊዜና ወጪን የያዘ የዜጎች ቻርተር በማዘጋጀት ለአገልግሎት ፈላጊ ዜጋ ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል። ሌላው ከተቋም የበላይ አመራር የሚጠበቅ ሥነምግባራዊ ተግባር ነው።

የተቋም የበላይ አመራር የሚጠበቅበትን የአመራር ሥነምግባር መርሆዎችን ተከትሎ የማይመራ ከሆነ በሚወስናቸው ውሳኔዎች የሚዋዥቅ፣ ጠንካራ አቋም ከሌለው፣ የአመራር ብቃትና ከህሎት ካልያዘ፣ በተቋም ሥራ ላይ ተገቢውን ክትትል የማያደርግ ከሆነ በተቋም ውስጥ ያሉ ተከታዮች/ሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች/

እምነት ስለማይጥሉ በተቋም ውስጥ ለራስ ጥቅም እንጅ ለህብረተሰብ ጥቅም መሥራት ቅድሚያ አይሰጡትም። ይህም የሌበነት አስተሳሰብ እየገነነ ይሄድና ተቋሙን ለውጤት አልባነት እየዳረገ ይሄዳል።

በመጨረሻም የተቋም አመራር ግልጽ ርዕይ በመንደፍ በግልጽነትና በተጠያቂነት አሠራር በቁርጠኝነት ስሜት ተቋሙን ሥነምግባራዊ የአመራር መርሆዎችን በመከተል መምራት ከቻለ በተቋም ውስጥ ሊፈጸም የታሰቡ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ድርጊቶችን እንዲቀንሱ ከማድረጉም በላይ የህዝብንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል የህዝብ ፍላጎት በማርካት ተቋሙንና ሀገሪቱን ውጤታማ ያደርጋል። ነገር ግን ተቋም ውስጥ የተከታዮች የመፈጸም አቅም በመገንባትና ለሥራ የሚያነሳሱ ተግባራት ሳይፈጸም የአመራር ሥነምግባር መርሆዎችን የሚጣረሱ ተግባራት የሚያከናውን ከሆነ ተቋሙ ውስጥ ተከታዮች/ ሥራ ኃላፊና ሰራተኞች/ የተቋም ርዕይ ለማሳካት ሳይሆን ለራሴ በሚል መርህ በመንቀሳቀስ ሙስና እና ብልሹ አሠራር የመከላከል ሚና ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ።

ከሙስና ምርመራ ...

መጠቀሱን ፋና ዘግቧል።

በዚህ መልኩ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 ሀ እና ለ የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ተደራራቢ የማታለል የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቧባቸዋል።

ተከሳሾቹ በዛሬው ቀጠሮ ክሱ ከደረሳቸው በኋላ የዋስትና መብታቸው እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል።

ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ÷ የተከሰሱበት አንቀጽ ዋስትና እንደማያስፈቅድ ጠቅሶ የተከራከረሲሆን ፍርድ ቤቱ መርምሮ የዋስትና ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረግ ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ አዟል።

በሌላ የሙስና ወንጀል መረጃ በአዲስ አበባ በግሪክ የኮሚዩኒቲ ትምህርት ቤት ላይ በወንጀል ጥርጣሬ በደረሰ ጥቆማ ምርመራ መጀመሩን የፍትሕ ሚኒስቴር ገለጸ።

የትምህርት ሂደቱ እንዳይስተጓጎል አዲስ አስተዳደር ተሹሞ ሥራ መጀመሩም ተገልጿል። ፍትሕ ሚኒስቴር የትምህርት ቤቱ የቀድሞ ቦርድና አስተዳደር ከተለያዩ ወንጀሎች ጋር ተያይዞ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በደረሰ ጥቆማ መሰረት የወንጀል ምርመራ መጀመሩን አስመልክቶ መግለጫ ሰጥቷል።

በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በወንጀል የተገኘ ኃብት ምርመራና ማስመለስ ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዳይሬክተር ጸጋ ዋቅጅራ፥ በግሪክ የኮሚዩኒቲ ትምህርት ቤት ላይ የወንጀል ምርመራ መጀመሩን ገልጸዋል። የወንጀል ምርመራው የተጀመረው የቀድሞ ቦርድና አስተዳደር በወንጀል ድርጊት ተሳትፈዋል በሚል በመጠርጠራቸው መሆኑን ተናግረዋል።

የተለያዩ የወንጀል ጥርጣሬዎች መኖራቸውን ገልጸው፥ ከዚህ መካከል በወንጀል የተገኘ ኃብት እንዳይሸሽ ለማድረግ ትኩረት መደረጉን ጠቁመዋል። ለጊዜው መጠኑ ያልታወቀ ከፍተኛ ገንዘብ በወንጀል ድርጊት ተገኝቷል የሚል ጥርጣሬ በመኖሩ፥ ገንዘቡ ወደ ተለያዩ አካላት እንዳይሸጋገር፣ በትምህርት ቤቱና በማኅበረሰቡም ላይ ጉዳት እንዳይደርስና ለሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች አስተዳደር መሾሙን ተናግረዋል።

አዲስ የተሾመው አስተዳደር በሙስና ወንጀል ልዩ ሥነ-ሥርዓት ሕግ 434/1993 አዋጅ መሰረት ለፍትሕ ሚኒስቴርና ለፖሊስ በተሰጠ ሥልጣን መሰረት መሆኑን ጠቅሰዋል። የተሾሙት አስተዳዳሪዎች ንብረቱን በጊዜያዊነት ተረክበው የወንጀል ክስና ምርመራው ተጠናቆ የመጨረሻ ውሳኔ በመዝገቡ እስኪገኝ ድረስ ንብረት እንዲጠብቁና እንዲያስተዳድሩ መሾማቸውን አስረድተዋል።

አስተዳዳሪዎቹ ንብረቶቹን ከማስተዳደር ባሻገር የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዳይስተጓጎል ትምህርት ቤቱን እንዲመሩ ከቀድሞ የትምህርት ቤቱ ቦርድ ሥራ መረከባቸውንም ገልጸዋል። ለግሪክ ትምህርት ቤት ጊዜያዊ አስተዳደር ሆነው ከተሾሙት መካከል ጌታቸው ተፈራ፥ አዲሱ አስተዳደር ወደ ስራ መግባታቸው ተገልፃል።

በሌላ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መረጃ ቃቤ ህግ በከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ባቀረበባቸው የቀድሞ የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትር ጫላ ዋታ(ዶ/ር) መዝገብ ዝርዝር ላይ ተጨማሪ ሌሎች ድርጅቶችን በክሱ ላይ አካቶ ለመቅረብ ፍርድ ቤቱን ጠየቀ።

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ዐቃቤህግ ሌሎች በክሱ ያልተካተቱ ድርጅቶችን አካቶ ለማቅረብ ያቀረበው የክስ ዝርዝር ማሻሻያ ጥያቄን ለመጠባበቅ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

በግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም በነበረ ቀጠሮ ዐቃቤህግ የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ የቀደሞ ፕሬዚዳንትር ጫላ ዋታ (ዶ/ር) ጨምሮ 15 ተከሳሾች ላይ ከ 195 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት ማድረስ በሚል አራት ተደራራቢ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶ እንደነበር መዘገባችን ይታወሳል።

ክሱ ተመስርቶባቸው ከነበሩ ተከሳሾች መካከል የቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ የቀደሞ ፕሬዚዳንት ጫላ ዋታ(ዶ/ር)፣ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ታምሩ አኖሌ፣ የዩንቨርሲቲው የአስተዳደር እና የተማሪዎች አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ሮባ ደንቢ(ዶ/ር)፣ በዩኒቨርሲቲው የቢዝነስና ተቋማዊ ልማት ም/ፕሬዚዳንት ኢንጂነር አብርሐም ባያብል ይገኙበታል።

ይሁንና የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤህግ በክስ ዝርዝሩ ላይ ከተከሳሾቹ በተጨማሪ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው ሌሎች ድርጅቶችን አካትቼ ክሴን አሻሽዬ ለማቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጠኝ በማለት ፍርድ ቤቱን ጠይቋል።

በዚህም መሰረት ችሎቱ ዐቃቤህግ ሌሎች በክሱ ያልተካተቱ ድርጅቶችን አካቶ ለማቅረብ ያቀረበው የክስ ዝርዝር ማሻሻያ ጥያቄን ለመጠባበቅ ለሀምሌ ፲፩ ቀን 2015 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷል።

እንደ አጠቃላይ በ15 ተከሳሾች ላይ በግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም በተከሳሾቹ ላይ ቀርቦባቸው የነበረው የክስ ዝርዝር ላይ እንደተመላከተው በሰኔ 10 ቀን 2012 ዓ.ም በቀጥታ ግዢ እንዲፈጸም ውሳኔ በማስተላለፍ ከሌሎች ተከሳሾች ከስራ ተቋራጮች ያለአግባብ ካለ ግልፅ ጨረታ የግዢ በመፈጸም በመንግስት ላይ 195 ሚሊየን 52 ሺህ 812 ብር ከ81 ሳንቲም ጉዳት አድርሰዋል በማለት ነበር ዓቃቤ ህግ በዋና በልዩ ወንጀል ተካፋይ በመሆን ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል ተደራራቢ የሙስና ወንጀል ክስ ያቀረበባቸው።

በየትኛውም ቦታ ሆነው፣ በገጠርና በከተማ፣ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ሆነው በመንግሥት እና ሕዝብ ተቋማት እና በልማት ድርጅቶች እንዲሁም ከኢትዮጵያ በሙስና የሸሹ ሀብቶችን መረጃና ማስረጃ ካገኙ ይጠቁሙ።



ሀሳብ ያለህ ....

ሳቅና ደስታ .....

ከሁለት ሰዎች በላይ ሆነው ሲሰበሰቡ ሁሉም ሰው ሀሳብ ማቅረብ ይፈልጋል። ሁሉም ሰው ሀሳቡን ሲያቀርብ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ሀሳቡን ለመስማት ፍላጎት ያሳያሉ። ሀሳብ ማቅረብ ማለት ሀሳብን ለሌሎች ሰዎች ማካፈል ማለት ነው። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን አመለካከት ለሌሎች ሰዎች እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን ግንዛቤ ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን ስሜት ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን ፍላጎት ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን ልምድ ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን ችሎታ ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን እውቀት ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል።

ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን አመለካከት ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን ፍላጎት ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን ስሜት ለሌሎች ሰዎች ለማሳወቅ ያስችላቸዋል። ሀሳብ ማቅረብ ሰዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን ግንዛቤ

መልካም ዜጋ

«በአደኩበት አካባቢ፣ ከዚያ ሰው ፈቃድ ውጪ የሰውን ገንዘብ መውሰድ ትልቅ ሀጥያት ነው» - አቶ አማረ ታደሰ

በባለፈው የግንቦት ወር እትማችን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኛ የሆኑት አቶ አማረ ታደሰ፣በጥቅቱ መዘገባችን ታወሳል። የአቶ አማረ ታሪክ በብዙ አስተማሪ ይሆናል ብለን በማሰብ ዘርዘር ያለ ሀተታ ለናቀርብላችሁ ወደድን፡፤ አቶ አማረ በተለያየ ጊዜ በጥሬ ገንዘብ እና በቼክ በአጠቃላይ 436 ሺህ የአሜሪካ ዶላር በሚሠሩበት ስፍራ ተረስቶ በማግኘት ለባለቤቱ መመለሳቸውን ይናገራሉ። ይኹን እንጂ በዚሁ በጎ ሥራቸውን የወደዷቸው እና ድርጊቱን ያደነቁላቸው የመኖራቸውን ያህል ድርጊቱን እንደ ሞኝነት የቆጠሩም እንዳሉ አቶ አማረ ታደሰ ተናግረዋል። “ጓደኞቼም ሆኑ ዘመድ እንዲሁም 95 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ‘አንተ የማትለወጥ ሰው ነህ፤ አያልፍልህም፤ ለምን ትመልሳለህ?’ ብለውኛል” በማለት ያጋጠማቸውን ይናገራሉ።

‘መሠረቴ ያደግኩበት ሁኔታ ነው’ አቶ አማረ ታደሰ የ56 ዓመት ጎልማሳ ሲሆኑ፤ በአሁኑ ወቅት በቦሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓለም አቀፍ የመንገደኞች ተርሚናል ቢዝነስ ክላስ ላውንጅ ውስጥ ከፍተኛ አስተናጋጅ በመሆን እየሠሩ ናቸው። አቶ አማረ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በዚሁ መሥርያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

“የመጀመርያዎቹ አስር ዓመታት የሠራተኞች ካፍቴሪያ ውስጥ ነው የሠራሁት። የዛሬ 22 ዓመት ደግሞ ላውንጅ ውስጥ መሥራት ጀመርኩ” በማለት ስለሥራቸው ያስረዳሉ። በዚሁ የሥራቸው ባህሪ ምክንያት ከተለያየ አገራት የሚመጡ መንገደኞች ጋር እንደሚገናኙ እና በርካታ ዕውቀትን ከእነርሱ ማግኘታቸውን የሚናገሩት አቶ አማረ፣ አንዳንድ መንገደኞች የተለያዩ እቃዎችን በመርሳት እንደሚሄዱ ያስታውሳሉ።

“እኛ ብዙ ነገሮችን እናገኛለን። ሞባይል፣ የኪስ ቦርሳ፣ የማይገኝ ነገር የለም። እነዚህን ሁሉ ታድያ ወድቀው የሚገኙ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ስፍራ ላይ እናስቀምጣለን” በማለት ተረስቶ የሚያገኙትን እቃ እንዴት አንደሚያስተናግዱ ይናገራሉ።

ያገኙትን ወይንም የተረሳ እቃን ለባለቤቱ መመለስ ባህላቸው እንዳደረጉ እና ለዚሁ ደግሞ የአስተዳደግ ሁኔታቸው መሠረት እንደሆናቸው የሚናገሩት አቶ አማረ፣ “በአደኩበት አካባቢ፣ ከዚያ ሰው ፈቃድ ውጪ የሰውን ገንዘብ መውሰድ ትልቅ ሀጥያት ነው” ይላሉ።

“እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ጥቅምት 6/2010 ከናይጄርያ ወደ ቻይና እየተጓዘ የነበረ ነጋዴ፣ 200 ሺህ ዶላር የያዘ ቦርሳውን ረስቶ ሄደ” በማለት አቶ አማረ ታደሰ እንዲታወቁ ያደረጋቸውን ገጠመኝ ያስታውሳሉ።

“ላውንጁ ውስጥ እየተመላለስኩ ባለሁበት ወቅት ነበር ይህንን ቦርሳ ያገኘሁት። ከፍቼ ስመለከተውም ዶላር ውስጥ እንዳለ ተገነዘብኩ። ለአንድ ሰዓት ከግማሽ ያህል የገንዘቡ ባለቤት ሳይመለስ ሲቀር ለአለቆቼ ሰጥቼ ልወጣ እየተሰናዳሁ ባለሁበት ወቅት የገንዘቡ ባለቤት ተመልሶ መጣ።”

ከዚያም በኋላ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ገንዘቡ የናይጄርያዊው ነጋዴ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ለመንገደኛው ገንዘቡን እንደመለሱ አቶ አማረ ተናግረዋል።

ይህም ተጓዥ በትልቅ ድንጋጤ ውስጥ እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ አማረ፣ “ሰውየው ገንዘቡን የሚያገኝ አልመሰለውም ነበር። ማመንም አቃተው፤ ስለዚህም በጣም በመደነቅ ተሞላ። ‘የኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም ሕዝብ ነው፤ ድርጅቱም መልካም ድርጅት ነው’ በማለት አድናቆቱን ገልጾ ነበር” ይላሉ የነበረውን ሁኔታ ሲያስታውሱ።

ለዚሁ ተግባራቸውም የአፍሪካ ድንቃድንቅ መዝገብ ‘አቶ አማረ በሚሠሩበት ቦታ ተጥሎ ያገኙትን 200 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ለመሥሪያ ቤታቸው በመመለሳቸው የአፍሪካ ድንቃ ድንቅ መዝገብ የክብር አባልነት የምስክር ወረቀት ሰጥተናቸዋል’ ሲል ሚያዚያ 23/2015 ዓ.ም የምስክር ወረቀት ሰጥቷቸዋል።

‘ብላክ ቤሪ ስልኩን ሸለመኝ’

አቶ አማረ ስለሌላ ገጠመኛቸው ሲናገሩ ቀኑን በትክክል አያስታውሱም። ይኹን እንጂ በዚያን ወቅት የሞባይል ስልክ በኢትዮጵያ ውስጥ እምብዛም ያልተስፋፋና እንደ ትልቅ ነገር የሚታይበት ወቅት እንደነበር ያስታውሳሉ።

አንድ ቀን በሥራ ቦታቸው ላይ እያሉ 234 ሺህ ዶላር የተጻፈበት ቼክ እና 2000 ዶላር ጥሬ ገንዘብ የያዘ ቦርሳ ማግኘታቸውን ይናገራሉ። “ሰውየው ወደ አሜሪካ ሊጓዝ ነበር። በሚገባ አይቸው ስለነበር እርሱ ሊሳፈርበት ወደነበረው አውሮፕላን ሮጬ በመሄድ ሰጠሁት። ሰውየውም በጣም ተደንቆ ‘ከሳምንት በኋላ እመለሳለሁ እና ምን ይገፍልህ ልምጣ ብሎ ጠየቀኝ። “እኔም ሞባይል አምጣልኝ አልኩት። በዚያኑ ቅጽበት ከስልኩ ውስጥ ሲሙን በማውጣት የራሱን ብላክ ቤሪ ስልክ ሸልሞኝ ሄደ” ይላሉ።

ገንዘብ የሰው ልጅ ሠርቶ ማግኘት የሚችለው ነገር መሆኑን የሚናገሩት አቶ አማረ፣ እምነት ግን የሁሉ ነገር መሠረት በመሆኑ ወድቆ ያገኙትን ነገር በሙሉ መልሰው ለባለቤቱ እንደሚሰጡ ይናገራሉ። ይኹን እንጂ ጓደኞቻቸውም ሆኑ ዘመዶቻቸው እንዲሁም አብዛኛው የሚያውቃቸው ማኅበረሰብ፣ ‘አንተ መቼውንም አትለወጥም፤ ለምንድን ነው የምትመልሰው?’ በማለት እንደሚወቅሷቸው እና በዚሁ ድርጊታቸው ያዘኑና የተቆጡ እንዳሉ ይናገራሉ።

“ማኅበረሰቡ ጠልቶኛል ማለት እችላለሁ። እኔ የምፈልገው ግን በመጀመርያ የድርጅቱን ሕግ ማክበር ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እምነቴንና ፈጣሪዬን ማክበሬን ነው። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ቤተሰቦቼ በሥራዬ ወይንም በባህርዬ ከተደሰቱ ሌላው ለእኔ ምንም አይደለም” ይላሉ።

አክለውም “የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሕግ፣ ያንተ ያልሆነን ነገር አትውሰድ ይላ፤ ይህ ደግሞ ትክክለኛ መመርያ እና ሰውን የሚያስደስት ነው” ብለዋል አቶ አማረ። በሚያደርጉት ድርጊትም የማይፀፀቱ መሆኑን በመጥቀስ “እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ፤ የተለየ ስሜት ነው የሚሰማ፤ እቃውን ረስቶ ለሄደ ሰው ስመልስ በጣም ደስታ ይሰማኛል” በማለት አብሯቸው ያደገው ባህሪ የደስታቸው ምንጭ መሆኑን ይገልጻሉ።

አቶ አማረ ታደሰ 200 ሺህ ዶላር ከሚሠሩበት ስፍራ አግኝተው ለባለቤቱ መልሰዋል የሚለው መረጃ በማኅበራዊ ሚደያ ላይ በስፋት በተሰራጨበት ወቅት አንዳንድ ሰዎች ‘እንዴት አንድ ሰው 200 ሺህ ዶላር ይዞ ወደ አየር መንገድ ሊገባ ቻለ’ በማለት ጥያቄ ሲያነሱ ተስተውሏል።

አቶ አማረ በበኩቸው አንዳንድ መንገደኞች አየር መንገዱን ተጠቅመው ወደ ሌላ ሀገር በሚበሩበት ወቅት፣ ከአየር መንገዱ ውስጥ ሳይወጡ ወደ ሌላ ሀገር ሲጓዙ፣ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ከአገራቸው ይዘውት የመጡትን ገንዘብ ይዘው መጓዝ እንደሚችሉ አስረድተዋል።